“አዲሱ ቴሌ” እና የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት ኤጀንሲ (ኢንሳ)፡

የህወሃት/ኢህአዴግ የስለላ መረብ

ከውስጥ አዋቂዎች የተገኘ ግርድፍ መረጃ!!

በአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ የተዘጋጀ
ሚያዚያ 2004ዓም

ምስጋና

ይህንን ጽሁፍ በምናዘጋጅበት ጊዜ መረጃ በመስጠት የተባበሩን አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያንን ከልብ እናመሰግናለን፡፡ ጽሁፉ ካለው ምስጢራዊነት አኳያና ለደኅንነታቸው ስንል የግለሰቦቹን ስም ባንጠቅስም ግብራቸውን ግን ታሪክና ሕዝብ ሲያስታውሰው ይኖራል፡፡ በተለይ ግን ቴክኒካዊ ምክርና አስተያየት በመስጠት የረዱንን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያ ዶ/ር አዚዝ ሙሐመድን ከልብ እናመሰግናለን፡፡

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የተጠቀምንባቸውን አዳዲስ የቴክኖሎጂ ቃላትን እንደ ጸዳቤ (ኢሜይል) የመሳሰሉትን የወሰድነው ዲባቶ (ዶ/ር) መስፍን አረጋ "ሰገላዊ አማርኛ" በሚል ርዕስ ካሳተሙት መዝገበ ቃላት በመሆኑ ለእርሳቸውም ምስጋናችን እንገልጻለን፡፡ ሌሎች ቃላቶችን ከተለያዩ ድረገጾች ያገኘን ሲሆን አንዳንዶችንም ከእንግሊዝኛ-አማርኛ መዝገበቃላት ድረገጽ (https://amharicdictionary.com/) ላይ የተወሰዱ በመሆናቸው የድረገጾቹን ባለቤቶች ልናመሰግን እንወዳለን፡፡

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ የተጠቀሰው አስተያየት፣ ሃሳብና ማጠቃለያ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ ነው እንጂ ይህንን ጽሁፍ በማዘጋጀት ላይ የተባበሩንን ግለሰቦች የሚመለከት አይደለም፡፡

አዘጋጅ፡ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ የሚዲያና የሕዝብ ግንኙነት ግብረኃይል፡፡

አሳታሚ፡ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን) ነው፡፡ ይህ የጋራ ንቅናቄ **"ከጎሣ ይልቅ ለሰብዓዊነት ቅድሚያ እንስጥ"** በሚልና **"ሁላችንም ነጻ ካልወጣን ማንም ነጻ ሊሆን አይችልም"** በሚሉ መሪ መርሆዎች ኢትዮጵያውያንን ለሰላም፣ ለፍትህና ለዕርቅ እንዲቆሙ በማስተባበር አዲሲቷ ኢትዮጵያ ትመሠረት ዘንድ ለማኅበራዊ ፍትህ የቆመ ድርጅት ነው፡፡

Copyright © 2012 by The Solidarity Movement for a New Ethiopia (SMNE)

ይህንን ጽሁፍ ለማስተማሪነት፣ የቅስቀሳ ዘመቻ ለማካሄድ፣ ለጥናትና ምርምር እንደ ምንጭ በመጥቀስ ያለ ምንም ክፍያ መጠቀም ይቻላል፡፡

The Solidarity Movement for a New Ethiopia (SMNE)
910 17th St. NW, Suite 419
Washington, DC 20006 USA
Email: media@solidaritymovement.org
Website: www.solidaritymovement.org

ማውጫ

ምስጋና 2

1. መግቢያ 4

2. ዓላማ 5

3. ብሔራዊ የመረጃና ደኅንነት አገልግሎት (NISS) 7

4. ቱሌ ትልቁ የደኅንነት ተቋም 13

5. በአዲሱ ቱሌ ውስጥ የተካተቱት እነማን ናቸው? 20

6. አዲሱ ቱሌና ኢንሳ፡ የተዋሃዱ የአፈና ተቋማት 22

7. ስለላ፡- በመያዶች፣ ኤምባሲዎችና ታዋቂ ተቋማት ላይ 27

8. የፖለቲካ ፓርቲዎች ስብሰባ ምሥጢር ነውን? 32

9. የመረጃ ጫካ ውስጥ ግቡ!! 35

10. “በስማችሁ በተመዘገበ ኮምፒውተር አትጠቀሙ” 37

11. ማጠቃለያ 43

የዝግጅት ክፍሉ ማስታወሻ 45

ዋቢ 46

የስዕል ዋቢ 46

1. መግቢያ

ኢትዮጵያን በተለያዩ አቅጣጫዎች በማፈን በቁጥጥር መዳፉ ውስጥ አስገብቶ እየገዛ የሚገኘው ህወሃት/ኢህአዴግ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአፈና ሥራውን ከማጠናከር አልፎ ዘመናዊ ወደ ማድረግ እየተሸጋገረ ይገኛል፡፡ ለዚህም ተግባሩ በዋንኛነት እየተጠቀመበት ያለው ብሔራዊ የመረጃና ደኅንነት አገልግሎት (ብመደአ) በእንግሊዝኛው ምህጻረ ቃል **NISS (National Intelligence and Security Service)** የሚባለውን መስሪያቤትና በቅርቡ የተቋቋመውን የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት ኤጀንሲ (ኢመደኤ) ወይም በእንግሊዝኛው **(Information Network Security Agency (INSA - ኢንሳ))**[1] በመባል የሚታወቀውን ድርጅት ነው፡፡ እንደ መረጃ ምንጮቻችን የሚጠቀመው ደግሞ በአዲስ መልክ እየተዋቀረ የሚገኘውን ‹‹ኢትዮ ቴሌኮም››ን ወይም በቀድሞ ስሙ የሚታወቀውን የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽንን ነው፡፡ አገዛዙ እስካሁን ድረስ ሲያደርግ እንደቆየው ሁሉ በእነዚህንም መስሪያ ቤቶች ለይስሙላ የተሾሙ “ባለሥልጣኖች” ቢኖሩም ዋናውን ሥራ የሚያካሂደው በየቦታው በሰገሰጋቸው ታማኞቹ ነው፡፡

ከላይ በተጠቀሰው ዋናው የስለላ መ/ቤት **(NISS)** ቁጥጥር ሥር የሚገኘው **የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ (ኢመደኤ/ኢንሳ)** በመረጃ መረብ ውስጥ የሚያልፉትን ማናቸውንም ጉዳዮች እየተቆጣጠረና እየተከታተለ ለዋናው የስለላና ደኅንነት መ/ቤት የሚያቀርብ፣ መገናኛዎችን የሚያግት፣ የቴሌኮም አገልግሎቶችን የሚጠልፍ፣ የሚተነትን ተቋም ነው። የዚህ ጽሁፍም ዋና ዓላማ ህወሃት/ኢህአዴግ ይህንን ተቋም በመጠቀምና ሥራውን በአዲስ መልክ እያዋቀረ ካለው ኢትዮ ቴሌኮም ወይም ‹‹አዲሱ ቴሌ›› ጋር በማቆራኘት በአገራችን ሕዝብ ላይ እየዘረጋ ያለውን የስለላ መረብ የሚመለከት ይሆናል።

[1] በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ለአጠራር እንዲያመች **NISS (National Intelligence and Security Service)** የሚባለውን መስሪያቤት **“የስለላ መ/ቤት፣ የደኅንነት መ/ቤት፣ የስለላና ደኅንነት መ/ቤት”** ወዘተ እየተባለ የተጠቀሰ ሲሆን **Information Network Security Agency – INSA** ግን እንደ እንግሊዝኛው **ኢንሳ** በማለት ተጠቅመናል፡፡

2. ዓላማ

ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን) የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት ኤጀንሲን (ኢንሳን) በተመለከተ መረጃ የማሰባሰብ ሥራ ሲሰራ ቆይቷል። በርካታ አጀንዳዎች በመያዝ የበኩሉን አስተዋጽዖ እያበረከተ የሚገኘው የጋራ ንቅናቄያችን፣ የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ በንጹህ ዜጎች ላይ እያካሄደ ያለው አፈና፣ የሰዎችን የተፈጥሮ ነጻነት በሚፈታተን መልኩ እያከናወነ ያለውን አስነዋሪ ተግባራት እጅግ የከፋና ከአገር አልፎ ዓለም አቀፍ ተቋማትን፣ ዲፕሎማቶችን፣ ኤምባሲዎችን፣ የርዳታና ሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶችን፣ ወደ አገር የሚገቡ የውጭ ዜጎችን (በተለይም የምዕራብ አውሮፓ፣ የካናዳና የአሜሪካ ዜግነት ባላቸው ላይ) የሚያከናውነው ክብረ ነክ የስለላ ተግባር ቅድሚያ የምንሰጠው ጉዳይ ሆኗል።

ገና ከጅምሩ የምዕራብ አገር የቴሌኮም ተቋማትን ዓይናቸውን ላፈር ያለው የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ አገር ውስጥ ገብተው እየተንቀሳቀሱ የሚገኙትን የምዕራብ አገር የቴሌኮም ኩባንያዎች ሥራቸውን በጅምር ጥለው እንዲወጡ ሲያደርግ ውሳኔው “የነጻ ገበያን የሚጻረር፣ የውድድር ስርዓትን የሚደፈጥጥ፣ ቴሌን ወደ ከፍተኛ የአፈና ተቋምነት የሚያሸጋግር” መሆኑን ባለሙያዎችና የወደፊቱ ትልም የገባቸው አገር ወዳዶች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የአዋጅ ያህል የተቃውሞ ድምጻቸውን አሰምተዋል።

በተከታታይ ያለማቋረጥ አፈናና እንግልት ሲደርስበት የነበረው የግሉ ፕሬስ እንዲሁም በርካታ ከጉዳዩ ጋር አግባብ ያላቸው ባለሙያዎች በዚህ ጉዳይ ላይ ትኩረት ሰጥተው ሲጽፉና ድምጻቸውን ሲያሰሙ መቆየታቸው ይታወቃል፡፡ በተለይም ደግሞ የሪፖርተር ጋዜጣ ቴሌ ወደ ግል ይዞታነት እንዲሸጋገር ወይም በከፊል የግል (ፕራይቬታይዝድ) መሆን እንዳለበት በመጠቆም ለሶስት ተከታታይ ዓመታት ሲሟገት በርካቶች በቴሌ ላይ የተጠነሰሰው ድግስ የተስተዋላቸው አይመስልም ነበር። መጨረሻ ላይ ግን የተፈራው ሁሉ ደረሰ። ቴሌ አገልግሎቱ መረጃ መሰብሰብ ሆነ። ሰዎች ገንዘባቸውን ከፍለው ከቴሌ የሚገዙት አገልግሎት በራሳቸው ላይ ጠላት የመግዛት ያህል ሆነ። በመሆኑም “አዲሱ ቴሌ” ይህንን የጀርባ ስለላ የሚያከናውንበት በቂ መንገድ ተመቻችቶ በአሁኑ ጊዜ ወደ ተግባር እየተሸጋገረ ይገኛል፡፡

ይህ ዘገባ ሁሉንም መስክ በመዳሰስ የተሟላ ነው ለማለት ባይቻልም በዋና ዓላማነት ለማስተላለፍ የሚፈልገው መልዕክት ህወሃት/ኢህአዴግ የአገዛዝ ዘመኑን ለማራዘም የመረጃና የደኅንነት ተቋማትን በመጠቀም ከአገር የሚወጣውንና ወደ አገር የሚገባውን እንዲሁም በአገር ውስጥ የሚተላለፈውን የመረጃ ፍሰት በምን ዓይነት መልኩ ለመቆጣጠር እንዳቀደ በተወሰነ መልኩ የሚያብራራ ነው፡፡ ይህንን ማወቁ ዋንኛ ጠቀሜታውም ሰብዓዊ መብትን ከማስከበር አንጻር የሚታይ ቢሆንም አዲሲቷን ኢትዮጵያ ለመመሥረት በሚደረገው ትግል በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ የሚገኘው ወገናችን ትግሉን በሚያካሂድበት ወቅት ሊያደርግ የሚገባውን ቅድመ ጥንቃቄ ለማስገንዘብ ከማሰብም አኳያ እንደሆነ እንዲታወቅልን እንወዳለን፡፡

3. ብሔራዊ የመረጃና ደኅንነት አገልግሎት (NISS)

በእንግሊዝኛው ምህጻረ ቃል NISS (National Intelligence and Security Service) በመባል የሚታወቀው የስለላ መ/ቤት በድርጅታዊ አወቃቀር፣ በሰው ኃይል፣ በቴክኒክ ብቃት፣ በግንዘብ ወዘተ በኢትዮጵያ ካሉት መ/ቤቶች በላቀ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው፡፡ ይህ በህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ ቁጥጥር ሥር የሚገኝ መ/ቤት አገዛዙ ለሥልጣኑ የሚያሰጉትን በሙሉ በማደን፣ በማሰስና በቁጥጥር ሥር በማዋል በአጠቃላይ ለህወሃት ህልውና ስጋት የሆነን ሁሉ ከመንገድ የሚያስወግድ ኃይል ነው፡፡

ይህ ድርጅት እንደ ማንኛውም ተቋም የራሱ የሆነ ድክመት ቢኖሩትም (በተለይም የቴክኖሎጂ እሴቶችን ከመጠቀም አኳያ) በከፍተኛ ፍጥነት እየተሻሻለና ፈጣን ለውጦችን እያካሄደ የሚገኝ ተቋም ነው፡፡ ተጠያቂነትን በተመለከተ ግን የህወሃት የቀኝ እጅ እንደ መሆኑና የቀድሞውን የህወሃት የደኅንነት መምሪያ የተካ ስለመሆኑ አሁን የሚከተለው አሠራሩ በግልጽ የሚያሳይ ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪነቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ወይም ለይስሙላ ለሚሠየመው ፓርላማ ሳይሆን በቀጥታ ለመለስ ዜናዊ መሆኑ እንዲሁም በተቋሙ ውስጥ በቋሚ ሠራተኛነት የሚያገለግሉትና ቁጥራቸው ከፍተኛ የሆነው የትግራይ ተወላጆች መሆናቸው የዚህ መ/ቤት ዋነኛ መለያዎች ናቸው፡፡

ይህ የስለላና የደኅንነት መዋቅር በበላይነት የሚመራው በብሔራዊ የደኅንነት ምክር ቤት ሲሆን የምክር ቤቱ ዋና አባላትና ኃላፊዎችም ጠቅላይ ሚኒስትሩ (መለስ ዜናዊ)፣ የውጭ ጉዳይ ሚ/ሩ (ኃይለማሪያም ደሳለኝ)፣ የጠ/ሚ/ሩ ቢሮ ዋና ኃላፊ (ሙክታር ከድር)፣ የመከላከያ ሠራዊት ዋና ኃላፊ (ሲራጅ ፈጌሳ)፣ የፖሊስ ኮሚሽን ዋና ኃላፊ (ወርቅነህ ገበየሁ)፣ የፌዴራል ጉዳዮች ዋና ኃላፊ (ሽፈራው ተክለማርያም) እና የራሱ የመረጃና ደኅንነት አገልግሎት ዋና (ጌታቸው አሰፋ) ኃላፊ በጥምረት በመሆን ነው፡፡

ስዕል1፡ ከግራ ወደ ቀኝ፤ ከላይ ወደታች፡- ጠቅላይ ሚኒስትሩ (መለስ ዜናዊ)[i]፣ የውጭ ጉዳይ ሚ/ሩ (ኃይለማሪያም ደሳለኝ)[ii]፣ የጠ/ሚ/ሩ ቢሮ ዋና ኃላፊ (ሙክታር ከድር)[iii]፣ የመከላከያ ሠራዊት ዋና ኃላፊ (ሲራጅ ፈጌሳ)[iv]፣ የፖሊስ ኮሚሽን ዋና ኃላፊ (ወርቅነህ ገበየሁ)[v]፣ የፌዴራል ጉዳዮች ዋና ኃላፊ (ሽፈራው ተክለማርያም)[vi]

በኦፊሴል የሚጠቀስ ባይሆንም የአቶ መለስ የቀድሞ የጸጥታ አማካሪ የነበሩት አቶ አባይ ፀሃዬ በደህንነት መዋቅር ውስጥ ያላቸው ስፍራ አሁን ድረስ እንደተጠበቀ ነው። በህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ ውስጥ ስልጣን ለይስሙላ የሚሰጣቸው ክፍሎች፣ ወይም አገዛዙ እንደሚያመቸው አድርጎ የሰራቸው ፓርቲ አባሎች (ከላይ በፎቶው የተጠቀሱትን ዓይነት) ወይም አመራሮች በደኅንነቱ መዋቅር ውስጥ መረጃ ለቅሞ ከማስረከብ የዘለለ ሚና የላቸውም። አቶ አባይ ህወሃት ለሁለት በተሰነጠቀና አደጋ ውስጥ በገባበት ወቅት ባከናወኑት "ስልታዊ" ተልእኮ "በፍጹም ታማኝ" ከሚለው ማህደር ውስጥ የተመዘገቡ በመሆናቸው ምንም እንኳን አሁን በሚኒስትር ማዕረግ የስኳር ጉዳዮች ዳይሬክተር ቢሆኑም እስካሁን የደህንነት መዋቅሩ ፊታውራሪ ስለመሆናቸው አሰራሩን የሚያውቁ ይናገራሉ።

በተመሳሳይ የአቶ መለስ ፅህፈት ቤት ኃላፊ የነበሩትና ዛሬ በኢህአዴግ ቢሮ ውስጥ ተመድበው እየሰሩ ያሉት አቶ ብርሃኑ አዴሎም በደኅንነት መዋቅሩ የደቡብ ክልል አደረጃጀትና አወቃቀር ውስጥ ከፍተኛ ኃላፊነት አላቸው። በግምገማ የ"ስኳር" ጉዳይ ተነስቶባቸው ለጊዜው ኢህአዴግ ቢሮ እንዲያርፉ ቢደረግም የደኅንነት መዋቅሩን አልተለዩትም። ስለ አቶ ብርሃኑ ድርጅታዊ ድር፣ ከዋና ባለሃብቶችና

ከአቶ መለስ ባለቤት ጋር ያላቸውን ግንኙነት የሚያውቁ እንደገለፁት እሳቸውም "ታማኝ" ተብለው የተያዙ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ወደፊት የምናብራራው በሙስና በመነከር የአገዛዙ ቀንበር ጎታቾች ከሆኑት መካከልም ናቸው። ከሁሉም በላይ ግብረ ሰናይ ድርጅቶችን በመሰለሉ ሥራ፣ ግብረሰናይ ድርጅቶችን ከሥራ ውጪ ያደረገውን የመያዶችን ሕግና የጸረ ሽብርተኛነት ህግ በማውጣት የተጫወቱት ሚና "ታላቅ" ተብሎ የሚጠራ በመሆኑ የተገመገሙበት ጉዳይ ተዳፍኖላቸው የደህንነትና የአፈና መዋቅሩን በመመገብ አሁን ድረስ አሉበት።

ስዕል2. ከግራ ወደቀኝ በሚኒስትር ማዕረግ የስኳር ጉዳዮች ዋና ዳይሬክተር አባይ ጸሃዬ[vii] እና ብርሃኑ አዴሎ[viii]

ከ1989 ዓም ጀምሮ የስለላና የደኅንነት መ/ቤቱ (NISS) ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ የፈሰሰበት የመዋቅርና የአሠራር ለውጥ እያካሄደ የሚገኝ ሲሆን በተለይም በሥሩ የሚገኙትን ሁሉንም መምሪያዎች በኮምፒውተር በታገዘ ቴክኖሎጂ አዋቅሯል። በመሆኑም ካለፈው የኮ/ል መንግሥቱ አገዛዝ የተረከባቸውን የደኅንነት ፋይሎችን (መረጃዎችን) በአዲስ የደኅንነት መረጃ ቋት (ዳታ ቤዝ) ውስጥ አከማችቷል። ይህ የመረጃ ቋት ዋናው ዓላማ የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ የግል ማኅደር መሰብሰብ ሲሆን በተለይም በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ አገዛዙን ይቃወማሉ ተብለው የሚጠረጠሩ ግለሰቦችን መረጃ የመሰብሰቡን ሂደት ዋንኛ ትኩረት የተሰጠው ነው።

በአወቃቀር ደረጃ ይህ የስለላ መ/ቤት በሦስት መምሪያዎች የተከፋፈለ ነው። እነርሱም፡-

- **የመጀመሪያው** የደኅንነትንና የመረጃ (ስለላ) መምሪያ፣
- **ሁለተኛው** የድንበር ቁጥጥር መምሪያና

- **ሦስተኛው** የጸረአሸባሪነት መምሪያ ናቸው፡፡ በዚህ መምሪያ ውስጥ እስላማዊ አክራሪነትን የሚከታተል የምስጢር መምሪያ የሚገኝ ሲሆን መምሪያው በፌዴራል ፖሊስና በክልል ፖሊስ አመራሮችና አስተዳደሮች ተዋቅሮ በአቶ ሃሰን ሺፋ ዋና ኃላፊነት የሚመራ ነው።

ስዕል3. በስለላውና በቁጥጥሩ ከፍተኛ ሚና ከሚጫወቱት አንዱ የፌዴራል ፖሊስ ዋና መ/ቤት[ix]

አራተኛ ደረጃ ባይባልም በየቀኑ የሚተነፈሱትንና አዲስ የሚባሉትን መረጃዎች ከታች በመሰብሰብ ሪፖርት የሚያቀርቡ የበታች ተዘዋዋሪ፣ 2400 የሚጠጉ እግረኛ

ቃፊሮች አለ። ባለስልጣናትንና ነጋዴዎችን የንግድ ኢጋርና የጥቅም ሽሪክ በማድረግ የሚመርዙትን ጨምሮ በዋናነት አየሩንና የመረጃ ድሮችን በሙሉ የሚከታተለው ተቋም የህወሃት/ኢህአዴግ የስለላና የአፈና አገዛዝ የጀርባ አጥንት ናቸው።

ከላይ የተጠቀሱት ሦስት መምሪያዎች በሥራቸው የተለያዩ ንዑሳን መምሪያዎችና ክፍሎች ያሏቸው ሲሆን ከእነዚህም ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የአገር ውስጥ ደኅንነት ዋና መምሪያ፣
- የውጭ ደኅንነት ዋና መምሪያ፣
- የቴክኒክ አገልግሎት ዋና መምሪያ (ይህ መምሪያ ከኢንሳ ጋር ግንኙነት ያለው ሲሆን ዋና ተግባሩም የመረጃ መረብን መቆጣጠርና መከታተል ነው)፣
- የምልመላና ሥልጠና መምሪያ፣
- የቴክኒክ መረጃ ዋና መምሪያ (ይህ መምሪያ በውጭ አገር በተለያዩ ቦታዎች የደኅንነት ሰዎች ያሉት ሲሆን ዋና ተግባራቸውም ለደኅንነትና ለስለላ ተግባር የሚውሉ የኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎችን ማፈላለግና መግዛት ነው)፣
- የደኅንነት ዋና መምሪያ፣
- የኢሚግሬሽንና የዜግነት ዋና መምሪያ፣
- የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ባለስልጣን፣
- የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት ኤጀንሲ (ኢንሳ - ይህ መ/ቤት በብሔራዊ የመረጃና ደኅንነት አገልግሎት ቁጥጥር ሥር የሚገኝ ሲሆን ቴሌኮሙኒኬሽንን ጨምሮ ከሌሎች የመረጃ ተቋማት ጋር በመተባበር በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መስክ ስለላ የሚያደርግ ዋንኛ ተቋም ነው)፡፡

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የዚህ የስለላ መ/ቤት ዋንኛ መምሪያዎች ሲሆኑ በተለይም የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት ኤጀንሲ - ኢንሳ - መረጃንና የመረጃ መረብን በተመለከተ ብቃት ያለውና ጥራቱን የጠበቀ መ/ቤት ሲሆን የአገሪቱን ልማት አውታሮች መጠበቅና ከጉዳት መከላከል ዋንኛ አገልግሎቱ ነው፡፡ ይህ ከውጪ የሚጠቀስለት ተግባር ሲሆን ሌላኛው የኢንሳ ተግባር የመረጃ መረብ

ደኅንነትን በተመለከተ የጥናት ማዕከል ሆኖ ማገልገል፣ በተለይም ከቴሌና ከሌሎች መ/ቤቶች በሚያገኘው መረጃ የስለላ መ/ቤቱን (NISS) እስኪበቃው በመረጃ በማጥገብ የህወሃት/ኢህአዴግን ጥቅም በማስጠበቅ የአገዛዙን ዕድሜ ከአደጋ መታደግ ነው። የስለላ መ/ቤቱ ከኢንሳ ከሚያገኘው መረጃ በተጨማሪ በአዲስ አበባ ዋና ዋና መንገዶች፣ በግልና በህዝብ ህንጻዎች፣ በትራፊክ መብራቶች ወዘተ ላይ የደኅንነት ካሜራዎችን በመትከል የሕዝቡን እንቅስቃሴ መከታተል ሌላኛው ተግባሩ ነው። ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ንዑሳን መምሪያዎችና ክፍሎች መካከል የመጀመሪያዎቹ ሁለት ክፍሎች አገዛዙ በሚያስቀምጠው የቅደም ተከተል መዘርዝር መሠረት መረጃ የሚሰበስብና የሚተነትን የስጋት ትንተና (threat analysis) ክፍል ያላቸው ሲሆን እነዚህ ክፍሎች በሙያው በተካኑ ሠራተኞች የተሞሉ ናቸው።

ስዕል4. ለትራፊክ ደኅንነት በሚል ሽፋን በአዲስ አበባ በተለያዩ ቦታዎች ከተገጠሙትና የስለላው መ/ቤት በቀጥታ ከሚቆጣጠራቸው ካሜራዎች አንዱ[x]

ይህ የስለላና የደኅንነት መ/ቤት እጅግ ግዙፍና በርካታ መምሪያዎች፣ ንዑሳን ክፍሎች ወዘተ ያካተተ በመሆን በተለያዩ አቅጣጫዎች የስለላ ተግባሩን በማከናወን ህወሃት/ኢህአዴግ በሥልጣን የሚቆይበትን የዕድሜ ማራዘሚያ ታማኝ በሆኑ ሠራተኞችና ኃላፊዎች ያከናውናል። በ"ነጻ አውጪነት" ስም እስካሁን ኢትዮጵያን እየገዛ የሚገኘው ህወሃት የዚህን መ/ቤት አመራር መጀመሪያ ላይ ለአቶ መለስ በጣም ቅርብ ለነበሩት አቶ ክንፈ ገ/መድኅን ነበር የሰጠው። በአሁኑ ጊዜ ይህ

የስለላና የደኅንነት መስሪያ ቤት የሚመራው በሚኒስትር ማዕረግ ሲሆን ዋና ኃላፊው ግማሽ ኤርትራዊ የሆኑት አቶ ኢሣያስ ወልደጊዮርጊስ እንጂ አገር የሚያውቃቸውና አቶ ክንፈ ገ/መድህንን የተኩት አቶ ጌታቸው አሰፋ አይደሉም።

ስዕል5. ኮ/ሎ ተስፋዬ ወልደሥላሴን የተኩት የቀድሞው የደኅንነት ኃላፊ አቶ ክንፈ ገብረመድኅን[xi]

4. ቴሌ ትልቁ የደኅንነት ተቋም

የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን የአገልግሎት አሰጣጡን ለማስፋትና ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም ሲነሳ በመጀመሪያ ፊቱን የሰጠው ለምዕራብ አገር የቴሌኮም ኩባንያዎች ነበር። ሞባይል፣ መደበኛ ስልክ (cordless home phone)፣ ብሮድባንድና ገመድ አልባ (wireless) የስልክ መስመሮችን ለመዘርጋት በተዋረድ ለተያዘው ዕቅድ እንደ ቅደም ተከተላቸው ፈጠረታ ሲወጣ አሸናፊዎች የነበሩት ኤሪክሰን፣ ኖኪያ፣ ሲመንስ፣ አልካቴል... የመሳሰሉት አንጋፋ የምዕራብ አውሮፓ የቴሌኮም ድርጅቶች ሲሆኑ አንድም የቻይና የቴሌኮም ኩባንያ አልነበረም።

ይህ እየሆነ ሳለ አቶ መለስ በድንገት ለጉብኝት ቻይና ደርሰው ሲመለሱ አዲስ ነገር ተሰማ። የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽንን ዘመናዊ ለማድረግ ዜድቲኢ[2] (ZTE: Zhongxing Telecommunication Equipment

[2] **ዜድቲኢ** በ1978ዓም አካባቢ የተቋቋመና በርካታ የቻይና ኮሙኒስት መንግሥት ተቋማት ከቻይናው የኤሮስፔስ ሚኒሰቴር መ/ቤት ጋር በመሆን የሚቆጣጠሩት ድርጅት ነው። የድርጅቱ ዋንኛ ምርት የሞባይል ስልክ ሲሆን በዚህም ምርቱ ከዓለም የ4ኛ ደረጃን ይዟል። ከዚህም በተጨማሪ ኦፕቲካል ትራንስሚሽን፣ የዳታ ኮሙኒኬሽን ጊር፣ የቴሌኮሙኒኬሽን ክትብቁስ (ሶፍትዌር)፣ ወዘተ ከሚጠቀሱት ምርቶቹ ጥቂቶቹ ናቸው።

Corporation) የተሰኘ የቻይና የቴሌኮም ኩባንያ 1.5 ቢሊዮን ዶላር ከቻይና ኤግዚም ባንክ (Exim Bank[3]: Export-Import Bank of China) ይዞ ወደ ኢትዮጵያ እንደሚገባ መናፈስ ጀመረ። ጉዳዩ ከቴሌ ጋር እየሠሩ ያሉትን የምዕራብ አገር ኩባንያዎች አስደነገጠ። በወቅቱ ለተፈጠረው ስጋት የተሰጠው መልስ "የዓለም ቴሌኮም ቴክኖሎጂ አንዱ ከሌላው ጋር እንዲግባባ ተደርጎ የሚሠራ ተመሳሳይ ቴክኖሎጂ በመሆኑ ስጋት ሊፈጥር አይገባም" የሚል ነበር። በሌላ ወገን ግን የቻይና የቴሌኮም ኩባንያዎች እንዲገቡ የተደረገው ቀደም ሲል ሲሰሩ የነበሩትን የቴሌኮም ኩባንያዎች በማግለል የምዕራብ አገሮችን የስለላ መዋቅር መሸሽ በህወሃት/ኢህአዴግ በድርጅት ደረጃ ስለታመነበት መሆኑ ተገልጿል።

ከሁለት አቅጣጫ መረጃዎች እየተስተናገዱ በነበረበት በዚህ ወቅት ስሙ እምብዛም የማይታወቀው የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ (ኢንሳ) እና ኃላፊው ወደ መድረክ ብቅ አሉ። ብዙም ሳይቆይ "መንግስት ባደረገው ስምምነት መሰረት የቻይናው የቴሌኮም ኩባንያ ዜድቲኢ በቬንደር ፋይናንሲንግ[4] (በሻጭ አበዳሪነት) 1.5 ቢሊዮን ዶላር ካገሩ ይዞ የመጣው ያገራችንን ኋላ ቀር የቴሌኮም አገልግሎት ቀልጣፋና ዘመናዊ ለማድረግ ታስቦ ነው" የሚል መግለጫ ራሱ ቴሌና የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስትሩ ተናገሩ።

ቴሌን ዘመናዊ ለማድረግ ቃል በመግባት ፕሮጀክቶቹ ሲጠናቀቁ ወይም ፕሮጀክቱ ከተጀመረ ከስምንት ዓመት በኋላ የሚከፈል 1.5 ቢሊዮን ዶላር ይዞ የመጣው ዜድቲኢ የመጀመሪያዎቹን የሙከራ አንቴናዎች እንደተከለ ችግር

---

[3] የቻይናን የውጪ ንግድ ማስፋፋት ቀዳሚ ተግባሩ በማድረግ በ1987ዓም የተቋቋመው **ኤግዚም ባንክ** የቻይና ኮሙኒስት መንግሥት የሚከተለውን የውጭ ንግድ፣ ዲፕሎማሲ፣ ወዘተ ፖሊሲ እንዲያራምዱ ከተፈጠሩ ሦስት ባንኮች አንዱ ነው። እጅግ ከፍተኛ የገንዘብ አቅም እንዳለው የሚነገርለት ይህ ባንክ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚ ትብብርና ልማት ስምምነቶችን (OECD) በሚጥስ መልኩ የሚያደርገው የትብብር ስምምነቶች (በተለይም ከታዳጊ አገራት ጋር) የበርካታ ምዕራባውያንን ወቀሳ እያስከተለበት ይገኛል። የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ በቴሌኮሙኒኬሽን ዘርፍ ከአፍሪካ ብቸኛ የሆነውን ግዙፍ ኢንቨስትመንት ከቻይና ኮሙኒስት መንግሥት ጋር ማድረጉ ዘርፉን ለማሳደግ ብቻ እንዳልሆነ የሚስተዋል ነው።

[4] በእንግሊዝኛ 'vendor financing' ተብሎ የሚጠራው አሠራር አበዳሪው ራሱ ሻጭ የሆነበት የንግድና የብድር አገልግሎት ነው። ይህም ማለት አንድ ድርጅት የሚሸጠውን ዕቃ ለገዢ በሚያቀርብበት ጊዜ ገዥው ዕቃውን ለመግዛት የገንዘብ ብቃት በማይኖረው ጊዜ ሻጩ ራሱ ገንዘቡን ለገዢው ያበድራል። ይህ ሲሆን ሻጩ ዕቃውን በመሸጥ ትርፍ የሚያገኝ ብቻ ሳይሆን ገንዘብ ከማበደርም የሚገኘውን ወለድ ይሰበስባል። በሌላ አነጋገር ሻጩ የራሱን ዕቃ መልሶ በመግዛት የራሱን የሸያጭ ገቢ ከፍ እንዲል ያደርጋል ማለት ነው። ይህ ዓይነቱ የንግድ አሠራር የራሱ የሆኑ ችግሮች ወይም በራሱ በሻጩ ላይ ጉዳት የማስከተል ባህርይ ቢኖረውም ብዙውን ጊዜ የሻጩን ጥቅም በማስጠበቅ የሚከናወን የንግድ ስምምነት ነው።

ተፈጠረ። የተለያዩ የቴሌኮም ኩባንያዎች የተከሏቸው አንቴናዎች (ቪሳቶች)[5] ሲገጣጠሙ ወይም አንዱ ከሌላው ኔትወርክ ጋር እየተሳሳመ ሲሰራ ዜድቲኢ የተከለው ቪሳት ሌሎችን "አላውቅም" አለ። ወዲያውኑ "ድርጅታዊ" ውሳኔ ተወሰነ። እነ ኖኪያ፣ ኤሪክሰን፣ አልካቴል፣ ሲመንስ ወዘተ የሰሩዋቸው አንቴናዎች ተነቅለው ወደ ግምጃ ቤት እንዲወረወሩ ታዘዘ። ዜድቲኢ እንደ ቀይ ኮከብ ዘመቻ ሌት ከቀን የመንቀልና የራሱን አንቴናዎች የመትከል ስራ ተያያዘ።

ውሳኔው አስደንጋጭ ቢሆንም ተግባራዊ መደረግ ሲጀምር ባለሙያዎች ተቃወሙ። የቴሌኮም ቴክኖሎጂ ዓለም ዓቀፋዊ መስተጋብሩን (ኔትወርክ) ካልጠበቀና ከሁሉም የቴሌኮም ኩባንያዎች ጋር መጣጣም ካልቻለ ለወደፊቱ አደጋው የከፋ እንደሆነ ተናገሩ። በሌላም በኩል ተወዳዳሪ ኩባንያዎች ኔትወርክ ተከፋፍለው ሲሰሩ ተጠቃሚ መሆን እንደሚቻልና ቀደም ሲል የተተከሉት ሲስተሞች የወጣባቸው ገንዘብ እጅግ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ በመሆኑ ኪሳራው የአገር እንደሆነ አሻዝ ተጠቅሶ መረጃው ቀረበ።

ስዕል6. በቀድሞ አጠራሩ የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ይባል የነበረው[xii]

[5] ቪሳት ወይም በእንግሊዝኛው very small aperture terminal (VSAT) የሳተላይት መገናኛን በመጠቀም ከምድር ጋር በዲሽ ከዚያም ወደተጠቃሚው መሣሪያ በአንቴና የማስተላለፊያ ዘዴ ነው፡፡ በ1990ዎቹ መጀመሪያ እንደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ያሉ በከፍተኛ ሁኔታ የመረጃ መረብ ተጠቃሚ የሆኑ ድርጅቶች ቪሳት ለማስገባት በተደጋጋሚ ቢሞክሩም ህወሃት "ሕግ የለም" በሚል ሲከለክላቸው ቆይቷል፡፡ በያዝነው ዓመት የጥቅምት ወር የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ሚ/ር እንደ አየር መንገድ፣ ንግድ መርከብ የመሳሰሉ መ/ቤቶች ቪሳትን መጠቀም የሚችሉበትን መመሪያ ከዓመታት ውትወታና ወቀሳ በኋላ ቢያወጣም መ/ቤቶቹን ለተጨማሪ ወጪ እየዳረጋቸው ያለው ይህ አካሄድ የዋንኞቹን መ/ቤቶች ቀልብ እንዳልሳበ ይነገራል፡፡

በቴሌ መጋዘኖች ውስጥ ያሉ መለዋወጫዎች ለቀድሞው ስርካት (system) ተብለው የተገዙ በመሆናቸው የምዕራቡ አገራት የቴሌኮም ኩባንያዎች የዘረጓቸውን የመስተጋብር ስርካቶች (network systems) ነቃቅሎ መጣል የሚያስከትለው ኪሳራ ብቻ ሳይሆን የቻይናው ኩባንያ የሚጠቀምበት መሳሪያ ጥራት የሌለው በመሆኑ አገሪቱን ወደፊት በመለዋወጫ ከፍተኛ ወጪ እንደሚያስወጣት ጥናት ቀረበ። በሻጭ አበዳሪነት ስምምነት 1.5 ቢሊዮን ዶላር ይዞ የመጣው ዜድቲኢ ፕሮጀክቱን ካስረከበ በኋላ ዕዳ መክፈል ሲጀመር ቴሌ ከሚሰበስበው ገቢ 60% የሚሆነው ለመለዋወጫ ግዢ የሚውል በመሆኑ ተቋሙ የኢትዮጵያ ሊባል እንደማይችልና የሠራውን ለቻይና እየገበረ እንደሚኖር "ደረታቸውን እየመቱ" የተናገሩ ዛሬ ቴሌን ተሰናብተው የበዩ ተመልካች ለመሆንና ለመሰደድ ተገደዋል።

ቀደም ሲል የተተከሉት የምዕራብ አገራት የቴሌኮም ቴክኖሎጂና መሣሪያዎች በተመለከተ የህወሃት/ኢህአዴግን ምስጢር ለመደበቅ የማያስችሉ፣ ይልቁኑም የምዕራብ አገሮችን አገዛዙ የሚፈጽማቸውን ተግባራት በቀላሉ ለማግኘት በማስቻል ተጠቃሚ ያደርጋቸዋል የሚል ትንታኔ ከህወሃት በኩል ተሰጥቶበት ነበር። የምዕራብ አገራቱ የቴሌኮም ተቋማት የገነቡት ቴክኖሎጂ ተነቅሎ እንዲጣል የተደረገው "ምንም ዓይነት መረጃ እንዳይወጣ ለማድረግ" በሚል በፓርቲ ደረጃ ስለታመነበት ነበር።

የምዕራብ አገሮች የቴሌኮም ኩባንያዎች የሚዘረጉት ቴክኖሎጂ ከስለላና ደኅንነት መረብ ጋር ተቆራኝተው ስለማይዘረጉ መረጃዎች እንዳያፈተልኩበት የሰጋው የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ ከደህንነት የመረጃ መረብ ጋር ተቆራኝቶና ተገምዶ የሚዋቀረውን የቻይናን የቴሌኮም ቴክኖሎጂ ለመጠቀም እንደወሰነ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል። አያይዞም አገዛዙ ካለት የአፈና መዋቅሮችና ከመሰረቱ ከነበረው የግራ ፖለቲካ አስተሳሰብ በመነሳት የሚያደርጋቸው የምስጢር ግንኙነቶች ከምዕራብ አገሮች የተሰወረ እንዲሆን በሚሊዮኖች በሚቆጠር ዶላር ወጪ ተደርጎ የተገነባውን የቀድሞ የቴሌኮም ቴክኖሎጂዎችን ሙሉ በሙሉ ለማስወገድ መወሰኑን ያገኘነው መረጃ ያብራራል። መሠረቱ የከረረ የግራ ፖለቲካ የሆነውና ለይስሙላና ለልመና ግን የምዕራባውያን ወዳጅ መስሎ የሚታየው ህወሃት ሊዘረጋ ለፈለገው የስለላና የአፈና መረብ የምዕራቡን ዓለም የቴሌኮም ኩባንያዎች አላመናቸውም፤ ስለሆነም የመነቃቀሉና የማፈራረሱ ውሳኔ ተላለፈባቸው።

ቴሌን ማሳደግ ሳይሆን ጠንካራ የአፈና ሥርዓት የመዘርጋት አጀንዳ የያዘው ህወሃት የሚሰነዘሩትን አስተያየቶች በሙሉ በጠላትነት እየፈረጀ “ከምዕራባዊያን ተለይ፣ ቻይናን ተከተል” የሚለውን መርህ ተሸክሞ የቴሌን የቀድሞ ስርካት (system) ማሰናከልና የቀድሞ ሠራተኞች የማፈራረስ ተግባሩን በዘመቻ ገፋበት። እንደተፈራው በሶስት ዓመት ተጠናቆ በስምንተኛ ዓመቱ እዳውን መክፈል ይጀምራል የተባለው የዜድቲኢ ፕሮጀክት ሳይጠናቀቅ ስምንት ዓመት አለፈው። የኢትዮጵያ የቴሌኮም አቅም እንኳን ሊያድግ መንግስት ከሌለባት ሶማሊያ እንኳን በማይሻል ደረጃ የሚገኝ ሆነ። ከሁሉም በላይ የሚያሳዝነው አዲስ የተመደቡት የቴሌ ሹማምንቶች ፕሮጀክቶች ሳይጠናቀቁ ርክክብ እየፈጸሙ ክፍያ እንዲከናወን መወሰናቸው ነው። በዚሁ በሙስና የሚፈጸም ክፍያ ቻይናዎቹ ይዘውት የገቡትን ዶላር መልሰው እንዲወስዱት እየተደረገ መጣ።

የዚህ ጽሑፍ መነሻና ዋንኛ ዓላማ ይህ ባለመሆኑ እንጂ ስለፕሮጀክቶች ስምምነትና ፕሮጀክት ሳይፈጸም በሚደረግ ርክክብ ቻይና የሂሳብ አካውንት ተከፍቶላቸው በሙስና የሚጨማለቁትን ክፍሎች መዘርዘር በተቻለ ነበር። የህወሃት/ኢህአዴግ ዓላማና ትኩረት አፈናን ማጠናከርና የአፈናውን መስተጋብር (ኔትወርክ) በራሳቸው ታማኝ ኃይል ማደራጀት በመሆኑ በባለሙያዎች ሲቀርቡ የነበሩትን ትችቶችና ምክሮች ወደ ጎን በመወርወር ዋናውን አጀንዳቸውን ለማስፈጸም ይሟሟቱ ገቡ።

“ካፈርኩ አይመልሰኝ” የሚለው የአቶ መለስ አገዛዝ “አዲሱ ቴሌ” በሚል አዲስ አስተዳደርና አዲስ ሠራተኞች ያቀፈ ቢሮ ማደራጀት ጀመረ። በዳግማዊ አጼ ምንሊክ የተቋቋመውና ከ100 ዓመት በላይ ያስቆጠረው ቴሌ ካልፈረሰ፣ ዓርማው ካልተቀየረና ሠራተኞቹ በአዳዲስ የህወሃት ሰዎች ካልተተኩ አዲሱ ቴሌ ግቡን ሊመታ ስለማይችል “አሮጌውን ቴሌ” የማፍረስ ተልዕኮ ያለው አዲሱ ቴሌ በምልመላ፣ በስልጠና፣ በአቅም ግንባታና አሮጌው ቴሌ ውስጥ ያሉትን ቁልፍ ሰራተኞች በመሰለል ሥራ ተጠመደ።

ስዕል7. አዲሱና[xiii] አሮጌው[xiv] የቴሌ መለያ ምልክቶች

“እናት አገር” እያለ የዜድቲኢን ፕሮግራም ለማሳካት የሚንከላወሱት የአሮጌው ቴሌ ሠራተኞች ጉዳዩና ድራማው የገባቸው አርፍዶ ነበር። ቴሌ ከኢንሳ ጋር መስተጋብሩ ከተወዳጀ በኋላ፣ የአዲሱ ቴሌ አዲስ አመራርና ተመሪዎች አቅም ከተስተካከለና አዲሱ ቴሌ አሮጌውን ቴሌ መዋጥ እንደሚችል ከተረጋገጠ በኋላ “እንደ ላም የምትታለብ” ሲባል የነበረውን ቴሌ አስተዳደሩን ለውጭው ኩባንያ የመስጠት ድራማ ይፋ ሆነ። ቴሌን ለማስተዳደር አሸነፈ የተባለው የፈረንሳይ ኩባንያ (ፍራንስ ቴሌኮም) ለሥራው አመቺ እንዲሆንለት እንደወሰነ በማስመሰል ቴሌን ከአገር ወዳዶች የማጽዳቱ ስራ ተከናወነ። በሺህ የሚቆጠሩ ሰራተኞች ተሰናበቱ። ወደፊትም ይሰናበታሉ። የፍራንስ ቴሌኮም የቴሌን ማኔጅመንት ተረክቦ ለሁለት ዓመት እንዲሰራ ውል በተፈጸመ ማግስት ስምንት ሺህ የሚጠጉ ባለሙያዎችና ሰራተኞችን አሰናበተ።

ፍራንስ ቴሌኮም የቴሌን ማኔጅመንት ከተረከበና ቴሌን ማስተዳደር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ጎን ለጎን የቴሌ መክሰር፣ የቴሌ ገቢ መቀነስ፣ የማኔጅመንቱ አቅም ማነስ በተጓዳኝ ይሰበክ ገባ። ይህ ሁሉ የሚደረገው ቴሌን ከአገር ወዳዶችና ከኢትዮጵያዊያን ባለሙያዎች የማላቀቅ ተግባር በስልትና በጥድፊያ በማከናወን የቀድሞውን ውጥን ተግባራዊ ለማድረግ ነበር።

ከዚህ በታች በሚታየው የፍራንስ ቴሌኮምና የኢትዮ ቴሌ ጣምራ ድርጅታዊ መዋቅር ላይ በኃላፊነት የተቀመጡት ግለሰቦች የብሔር ብሔረሰብ ተዋጽዖውን የሚወክሉ ናቸው ሊባል ቢችልም (ህወሃት ከተራ ክስ ለማምለጥ የሚጠቀምበት ዘዴ ነው) ዋናውን ሥራ ከጀርባ ሆነው የሚያከናውኑት የህወሃት ቁልፍ ሰዎችና በህወሃት አስተምህሮት የተጠመቁ ጥቅመኞች እንደሆነ ይስተዋላል።



ስዕል8. ለፍራንስ ቴሌኮም አስተዳደሩ የተሰጠው የቴሌ ድርጅታዊ መዋቅር[xv]

“ቴሌን እናጠራለን” በሚል አስመሳይ ዓላማ ከሠራተኛ ማኅበር አመራሮች ጋር ግንባር ፈጥሮ ሲሠራ የነበረው የህወሃት የመረጃ ቡድን ዓላማው ካልገባቸው የማኅበሩ አባላት አስፈላጊውን የማንነትና የጀርባ ታሪክ ምርመራውን አከናወነ። “ለደህንነታችሁ” በሚል የግል መኪናና መሳሪያ ተመድቦላቸው በሌሊት ሳይቀር ስብሰባ እየተቀመጡ ሲሠሩ የነበሩት “የቴሌ አገር ወዳዶች” በቴሌ የተንሰራፋውን ሙስናና ቅጥ ያጣ ግዢ ያጋለጡ መስሏቸው ለታዘዙት ሁሉ ጥራዝ እያዘጋጁ መልስ ሲሰጡ ቆዩና መጨረሻ ላይ ተጣለ፤ ተወረወሩ። አዲሱ ቴሌም ቀብራቸውን

አፋጠነላቸው። እነርሱን የሚተኩት ታማኞች መዘጋጀታቸው ከታወቀ በኋላ የአገር ወዳዶቹ "ቀብር" በአስቸኳይ ተጠናቅቆ ሲያበቃ "የአዲሱ ቴሌ" ምሥረታ ታወጀ፤ በዚህ መልኩ ቴሌ ወደ ደኅንነትና ስለላ ተቋምነት ተቀየረ።

5. በአዲሱ ቴሌ ውስጥ የተካተቱት እነማን ናቸው?

ዜድቲኢ ቴሌን ሲረከብ ዋናው ዓላማ የደህንነትና የስለላ መዋቅሩን ከአገሪቱ የቴሌኮም አገልግሎት ጋር ማዋሃድና የአፈናውን ስርዓት ዋስትና እንዲኖረው ማድረግ በመሆኑ የሰው ኃይሉን በህወሃት ታማኝ አገልጋዮችና አባሎች ማደራጀቱ አስፈላጊ ነበር። በዚሁ መሰረት 2000 (ሁለት ሺህ) የሚሆኑ ከከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ጀምሮ በልዩ እንክብካቤ ህወሃት/ኢህአዴግ እጅግ ከፍተኛ ገንዘብ ያፈሰሰባቸውና የተንከባከባቸው ታዳጊዎች የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ገብተው እንደተመረቁ ተመለመሉ። ከአዲስ አበባና ከመቀሌ ዩኒቨርሲቲ፣ ከመከላከያ ኢንጂነሪንግና ከተለያዩ ኮሌጆች፣ በትምህርታቸው ከፍተኛ ውጤት አላቸው የተባሉ የትግራይ ወጣቶችና ለማዛነቂያ ደግሞ በአቶ መለስና በህወሃት ስም የሚምሉ መሆናቸው የተረጋገጠላቸው የሌላ ብሔረሰብ አባላት የተዳመሩበት "አዲሱ ቴሌን" የመገንባቱ ሥራ ተጀመረ።

አዲሶቹን ምልምሎች ሲያሰለጥኑ የነበሩት በሰዓት በርካታ ዶላር የሚከፈላቸው የአሜሪካ የቴሌኮም ባለሙያዎች ከዓመት በላይ ስልጠና ከሰጡ በኋላ እስካሁን ምክንያቱ ግልጽ ባልሆነ ሁኔታ አዲሱን ቴሌ እውን ማድረግ እንደማይቻል ሪፖርት አቀረቡ። ብዙም ሳይቆዩ አዲስ አበባን ለቀቁ። ሁኔታውም የህወሃት/ኢህአዴግ ሰዎችን አስደነገጠ። ጉዳዩ ዜና እንዳይሆን የቴሌና ሌሎች የሚመለከታቸው ክፍሎች በእጅም በኃይልም ሃዱበትና አፈኑት።

ከዓመት በኋላ የፈረንሳይ ኩባንያ የቴሌን ማኔጅመንት እንዲይዝ ተደረገ። እነዚሁ ህወሃት በአምሳሉ የሠራቸውና ከልጅነታቸው ጀምሮ የህወሃትን ስትራቴጂ በልዩ መልኩ እየተጋቱ እንዲያድጉ የተደረጉት የአዲሱ ቴሌ ምልምሎች አዲስ ኮንትራት ከገባው የፈረንሳይ ድርጅት ጋር "ለማጅ" ተለጥፎባቸው አመራሩን

ተረከቡ። በዚህ መልኩ አሮጌ የተባለው ቴሌ ደህና ሰንብት ተባለ። ቁጥራቸው እጅግ በርካታ የሆነ የህወሃት ሰዎችና አባላት የተሰገሰጉበት “አዲሱ ቴሌ” ይባላል ተብሎ ቢጠበቅም ስልታዊ ማሻሻያ ተደርጎበት “ኢትዮ ቴሌኮም” የሚል ስያሜ ተሰጠው። ኢትዮ ቴሌኮም ያራገፈውን አራግፎ አዲስ ኃይል ይዞ ለመሥራት የተፈለገበት ዋና ምስጢር ተቋሙ ሙሉ በሙሉ ወደ ስለላና ደኅንነት ተቋምነት በመቀየር የህወሃት አባላትና በህወሃት ስውር አጀንዳ የተጠመቁ ካልሆኑ በስተቀር ሌሎች ሊታመኑ ስለማይችሉ ነው።

ስዕል9. በቅርቡ ስራቸውን አጠናቀው የሚሰናበቱት በኢትዮቴሌ የፍራንስ ቴሌኮም ዋና ስራ አስፈፃሚ ሚ/ር ገሬን ሚሼል ላትዩት[xvi]

በአንድ ሃገር ውስጥ የሚታመኑ፣ የማይታመኑ፣ ቢታመኑም ቁልፍ ኃላፊነት በነጻነት የማይሰጣቸው፤ ፍጹም ባይተዋር የሆኑና በጠላትነት ተፈርጀው የሚማቅቁ ዜጎች ይኖራሉ። ይህ ሁሉ የመብት ረገጣና ግፍ እንዲሁም በዘር ላይ የተመሠረተ ግልጽ መድልዎ እየተካሄደ “አገሪቱ ለሁሉም እኩል ነች፤ የብሔር ብሔረሰቦች እኩልነት በመፈቃቀድ ላይ ይመሰረታል” ይባላል።

6. አዲሱ ቴሌና ኢንሳ፡ የተዋሃዱ የአፈና ተቋማት

“በምርምር እና ስርፀት የተደገፉ የኢንፎርሜሽን ሴኩዩሪቲ አቅም በመፍጠር በመንግስት እና ህዝብ ቁልፍ የኢንፎርሜሽን እና ኢንፎርሜሽን መረብ ሊፈጠር የሚችልን ተጋላጭነት መከላከል”[6] በሚል ተልዕኮ እንደተቋቋመ የሚነገርለት የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ (ኢንሳ) (Information Network Security Agency (INSA) ዋንኛ ዓላማው “አገሪቱ በኢንፎርሜሽን፣ በኢንፎርሜሽን መረብና ቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶችን በብቃት እንድትጠቀም በማድረግ ሰላምንና ዴሞክራሲን እንዲሁም የልማት ስትራቴጂዎች የብሔራዊ ደኅንነት አደጋ ላይ በማይጥሉበት መልኩ ተግባራዊ እንዲሆን ማስቻል”[7] የሚል ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ይህ ከውጪው የመረጃ ልውውጥ ሲካሄድ ሊከሰት የሚችል ተጋላጭነትንና የሳይበር ሽብርተኝነትን ለመከላከል እንደፈጠረ የሚጠቀስለት ድርጅት መስተጋብሩን (ኔትወርኩን) ከፖሊስ፣ ከመከላከያ፣ ከደኅንነት፣ ከመገናኛ የመሳሰሉ መ/ቤቶች ጋር ማቆራኘት የመጀመሪያ ተግባሩ ነው፡፡ ይህንንም በመጠቀም ወደ አገር ውስጥ የሚገባውንም ሆነ ከአገር የሚወጣውን የመረጃ ፍሰት መቆጣጠርና ማፈን፣ በአገር ውስጥ የሚካሄደውን ማንኛውንም እንቅስቃሴ በመከታተልና በመተንተን የቅድሚያ ጥቃት እንዲካሄድ ለውሳኔ ማቅረብ በጥቂቱ የሚጠቀስለትና በአዋጅ ያልተደነገገለት “ሥልጣንና ተግባራቱ” ናቸው፡፡ በተለይ ግን የስለላ መረቡን ከአዲሱ ቴሌ ጋር በማቆራኘት የሚያከናውናቸው ተግባራት ማጋለጥ የወቅቱ አጀንዳ እንደሆነ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ የሚያምን በመሆኑ ወደፊት በስፋትና በጥልቀት ሊጠና የሚያሻውን ይህንን ጉዳይ በዚህ አጭር ዘገባ በማቅረብ ሕዝብ ቅድመ ጥንቃቄ እንዲያደርግ ማሳሰብ አስፈላጊ መሆኑን ያምናል።

በብርጋዴር ጄኔራል ተክለብርሃን ወልደአረጋይ የሚመራው፣ በቀጥታ ተጠሪነቱ ለአቶ መለስ የሆነውና የ“መንፈስ” ያህል የሚፈራው ኢንሳ፤ ዜድቲኢ

[6] http://www.insa.gov.et/INSA/faces/aboutinsa/aboutinsa.jsp?about=mission
[7] http://www.insa.gov.et/INSA/faces/aboutinsa/aboutinsa.jsp?about=objective

ከዘረጋው የቴሌኮም አገልግሎቶች ጋር በቀጥታ የተዛመደ ቴክኖሎጂ በቻይና ኮሙኒስት መንግስት አማካይነት በመታጠቁ፣ በዚሁ ቴክኖሎጂ አማካይት የአገሪቱን የመረጃ ፍሰት መቆጣጠር እንዲችል ተሞክሯል። በሌላ አነጋገር ነጻ ሞባይል፣ ነጻ መደበኛ ስልክ፣ ነጻ ኢሜል (ጸዳቤ)፣ ነጻ የፌስ ቡክና ተመሳሳይ አገልግሎቶች በህወሃት የስለላ መዋቅር ውስጥ እንዲወድቁ ተለፍቷል፤ እየተለፋም ነው። ምንም እንኳን ሙሉ በሙሉ ቁጥጥር ለማካሄድ የሚያስችግር ቢሆንም በነጻነት የሚተላለፉ መልዕክቶች ሁሉ የህወሃት የመረጃ ካዝና ውስጥ እንዲዘልቁ የአገር አንጡራ ኃብት ተከስክሷል፤ ያለማቋረጥ እየተከሰከሰም ነው። ኢንሳ ምን ያህል እንደተሳካለት ወደፊት ዝርዝር መረጃ ለማቅረብ ቃል የገቡት ወገኖችና ባለሙያዎች እንደሚሉት ከሆነ ከቴሌ አገልግሎት ተጠቃሚ የሚሆኑ ወገኖች ከጥንቃቄ ጉድለትም ይሁን ባለማወቅ የህወሃት/ኢህአዴግን የስለላ ኮሮጆ በየዋህነት እየሞሉ እንደሆነ አይሸሽጉም።[8]

ስዕል10[xvii]. በሽረሪት ድር የተመሰለው አዲሱ የኢንሳ አርማ፤ የቀድሞ አርማ

ወደዚህ የስለላ ኮሮጆ ውስጥ የሚገቡ መረጃዎች እንደ አስፈላጊነታቸው ይተነተናሉ። አንዳዶቹም እንደ ሁኔታው እየተቀጠሉና እየተበጠሱ ለፍርድ ቤት የፈጠራ ወንጀል ማስደገፊያነትና ማስረጃነት ይውላሉ። በኢንሳ ከሚገኙት መምሪያዎች መካከል "የስጋት ትንተና (Threat Analysis)" የሚባለው በዚሁ በመቀጠልና በመበጠስ ሥራ የተካነ ስለሆነ ከቤተሰብ፣ ከጓደኛ፣ ከትዳር አጋር፣

[8]የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደዘገበው (http://www.ethpress.gov.et/ethpress/main/news.php?newsLocation=home&newsInstruction=headline&newsId=7249) ከመጋቢት 27 ቀን 2004ዓም ጀምሮ በኢንሳ ትብብር ኢህአዴግ የመረጃ ፍሰቱን ወደ አንድ ቋት ለማስገባት (www.eprdf.org.et) የተሰኘ አዲስ ድረገጽ በ1ሚሊዮን ብር ወጪ አዘጋጅቶ ይፋ አድርጓል፡፡ ይህ በግልጽ የሚያሳየው ኢንሳ እንደ ፌዴራል መ/ቤትነቱ ለአንድ ፓርቲ ጥቅም ሳይሆን ለሕዝብ መቆም የሚገባው ሆኖ ሳለ በአንጻሩ ግን የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ ለራሱ የሥልጣን ማስረዘሚያ ያለአንዳች ተቀናቃኝ የኢትዮጵያን ኃብት እየመዘበረ መሆኑን ነው፡፡ አንድ የፌደራል መ/ቤት በምን ስሌት ነው ለአንድ ፓርቲ ያውም ሥልጣን ላይ ለተቀመጠ እንዲህ ዓይነት አገልግሎት የሚሰጠው?

ከከንፈር ወዳጅ፣ ከፍቅረኛ፣ ከሥራ ባልደረባ፣ ወዘተ በተለያዩ ወቅቶች የተደረጉ ምልልሶችን ወደኋላ በመመለስ ያገጣጥምና ለይስሙላ ለተቋቋሙት ፍርድ ቤቶች በማስረጃነት ያቀርባል፤ ንጹሃንም ይፈረድባቸዋል። በቅርቡ "አኬልዳማ" በሚል የተሰራው "የወንጀል ድራማ" የዚሁ መምሪያ "የሥራ ውጤት" ነው። በእነ ጄኔራል አሳምነው ጽጌ ላይም የተፈጸመው እንዲህ ያለው የቆርጦ ቀጥል ክስና ቃለመጠይቅ ነው።

አዲሱ ቴሌና ኢንሳ እየተመጋገቡ እንዲሰሩ ተደርጎ በሚዘረጋው መረብ ውስጥ ተጠቃሚ የሆኑ ሁሉ የሚቀያየሯቸው መረጃዎች ምስጢርነታቸው እንዲጠበቅ ኢንሳ ውስጥ በአመራር ላይ ያሉት ሰዎች የትግራይ ተወላጆች እንዲሆኑ መደረጉ የትምህርትና ሥራ ልምድ ብቃት ወይም የሜሪት ውጤት ወይም ሳይታሰብ የተፈጸመ ድርጊት ነው ለማለት አያስደፍርም። ቴሌ ውስጥም በተመሳሳይ ከስለላው አደረጃጀት ጋር በተያያዙት ቁልፍ መስተጋብሮች ውስጥ የትግራይ ወጣቶች እንዲመደቡ የተደረገ ሲሆን የቀድሞ ኃላፊዎች አገር ለቀው ወደ ደቡብ ሱዳንና ሌሎች አገራት ለመሰደድ ተገድደዋል።

ስዕል11. የመገናኛና ኢንፎርሚሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስትር፣ ቴሌን ከኢንሳና ከስለላው መ/ቤት ጋር በማዋቀሩ ሂደት ዋና አስተባባሪና የኢትዮ ቴሌኮም የቦርድ ሰብሳቢ ዶ/ር ደብረ ፅዮን ገብረ ሚካኤል[xviii]

ሞባይል ስልክን አስመልክቶ የሚመጋገበው የቴሌና የኢንሳ መረብ መረጃ የሚለቀመው በሶስት መንገዶች ነው።

- **አንደኛው** ባለሞባይሉ ጥሪውን ሲመልስ ወይም ጥሪ ልኮ ሲመለስለትና ሲያነጋግር፤
- **ሁለተኛው** በቀጥታ በራሱ ቁጥር ተጠልፎ ክትትል የሚደረግበት ሲሆን
- **ሶስተኛውና** አስገራሚው ባለሞባይል ስልኩ ተዘግቶ የሚደረጉ ማናቸውም ውይይቶች፣ ወጎች፣ የቤተሰብ ጨዋታዎች፣ የግል ምስጢሮች፣ ወዘተ ኢንሳ ጆሮ እንዲገቡ መደረጉ ነው።

በሌላ አነጋገር አንድ የተጠለፈ ሰው የሞባይል ስልኩ ተዘግቶ ስለተቀመጠ (በሞባይል ስልክ ስለማያወራ) መረጃ ማስተላለፍ አያቆምም ማለት ነው። (በተለይ አዲሱ ቴሌ ላለፉት ዓመታት አገልግሎቱን ያሻሻላል ተብሎ ሲጠበቅ ሞባይል ስልክ ሲሸጥ መክረሙ ያለ ምክንያት እንዳልሆነ እዚህ ላይ ልብ ይሏል።) መረጃውን ለጋራ ንቅናቄያችን ያስተላለፉት ክፍሎች "ማንም ሰው ስልኩን ሲያጠፋ ባትሪውን ከስልኩ ይለየው/ይንቀለው" ሲሉ ምክራቸውን ይለግሳሉ። አክለውም የተጠለፈ ወይም እንደሚጠለፉ የሚገምቱ ሰዎች ከዚህ መልዕክት በኋላ የሞባይል ስልካቸውን ለመረጃ መቀያየሪያ ለመጠቀም መሞከር የዋህነት እንደሆነ ይገልጻሉ። የድርጊቱንም አሳፋሪነት በአንድ ገጠመኝ ያስረዳሉ።

አንድ በተቃዋሚ ፖለቲካ እንቅስቃሴ ተሳታፊ የነበሩ ግለሰብ ስልካቸው ሙሉ በሙሉ በመረጃው መረብ ውስጥ እንዲወድቅ ሲደረግ እርሳቸው ምንም የሚያውቁት ነገር አልነበረም። እኚህ ግለሰብ እንደማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር በግል ስልካቸው የወደዱትን መልዕክት ሲያስተላልፉ ይቀዳሉ፤ ለማስረጃነትና ለስም ማጥፋትም ይመዘገባል። የፍቅርና የግል ማኅበራዊ ምስጢራቸው ሳይቀር ልቅም ተደርጎ ይቀዳል። በመጨረሻ ላይ የቀረበላቸው አንድ ጥያቄ "እርፊው ይቀመጡ" የሚል ነበር። በተለያዩ ወቅቶች ያደረጓቸውን የቃል ልውውጦች እየበጠሱ በመጠገንና ለማሸማቀቂያነት በመጠቀም የተቀነባበረውን ድምጻቸውን በሚቀርቧቸው ሰዎች አማካይነት እንዲሰሙ ተደረገ። በኋላም የተነገራቸው መልዕክት "የእርስዎ የሆኑ ሰዎች ድምጽዎን እየቀዱ ለመረጃ ሰዎች ይሰጣሉ፤ ማስረጃውም ይኸው ነው። ከእንግዲህ የተቃዋሚ ፖለቲካ እንቅስቃሴዎን ማብቂያ ቢያበጁለት ይሻላል፤ አለበለዚያ. . ." የሚል ነበር። የጋራ ንቅናቄያችን ባገኘው መረጃ መሠረት እንዲህ ያለው አስነዋሪ ተግባር በምስልም እየተዘጋጀ የተቃዋሚንም ሆነ ማንኛውንም

እንቅስቃሴ ለማገት ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ ይህ ደግሞ ራሱን የቻለ የጭራቆች ድርሰት ነው።

በተመሳሳይ በ1997 የቅንጅት አመራሮች የሚያደርጉት ስብሰባና የጉባዔ ክርክሮች አንዳንዴ በሚዘጉ የሞባይል ስልኮች፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ ብዕርና ሰዓት ወይም ወንበር ስር በሚለጠፉ የድምጽ መቅረጫዎች በመያዝ የድምጽ መረጃ ሲያቀብሉ የነበሩት በከፍተኛ ደረጃ ካለ የደኅንነት ባለስልጣናትና ከአቶ መለስ ጋር ግንኙነት ያላቸው የፓርቲው አመራሮች የሚፈጽሙት ክህደት እንደነበር የመረጃ ምንጮቻችን በዝርዝር አስረድተዋል።

አንድ ባለስልጣን፣ አንድ አባወራ/እማወራ፣ ፍቅረኞች ወይም የንግድ ሰዎች የሞባይል ስልካቸውን አጥፍተው አንድ ቦታ ሆነው የግል ጨዋታቸውን ቢያደሩ ሰዎቹ በተጠርጣሪነት በኢንሳ ዝርዝር ውስጥ ምልክት የተደረገባቸው ከሆኑ፣ የስልኩ ባትሪ እስካልተነቀለና ድረስ የሚያወሩትን ወሬ ወይም ቁምነገር ኢንሳ እንደ ሽገር ሬድዮ ሊሰማው ይችላል። ይህ ብቻ አይደለም አድራሻ ቀይረው እንኳን ቢቀመጡ የት እንዳሉ በሞባይላቸው አማካይነት በጂፒኤስ[9] ይታወቃል። አብዛኛውን ጊዜ የሚፈልጓቸውን ሰዎች ዱካ የሚከታተሉት በዚሁ ቴክኖሎጂ አማካይነት ነው። ይህ የኢንሳ ወይም የስለላ መረቡ ጥንካሬ ሳይሆን የሞባይል ተጠቃሚዎች የዋህነት ነው - በተለይም ሞባይላቸው አደጋ ውስጥ እንደሆነ የሚያውቁ!!

ከሁሉም አይነት የግንኙነት መስመሮች የመደበኛ ገመድ አልባ ስልክ (የቤት ውስጥ ገመድ አልባ ስልክ ወይም cordless home phone) አስተማማኝ ሆኖ

---

[9] በእንግሊዝኛው ምጻሕረ ቃል **ጂፒኤስ** (GPS - Global Positioning System) እየተባለ የሚጠራው በጎዋ የሚገኙ ሳተላይቶች በሚሰጡት መረጃ ቦታን እና ከጊዜ ጋር የተያያዙ የአየር ንብረትን የመሳሰሉ ሁኔታዎችን በየትኛውም የምድር ቦታ እንደሚከሰቱ ለመጠቆም የሚያገለግል ስርዓት ነው፡፡ ይህ የጂፒኤስ ፕሮግራም በዓለም ላይ ለሚገኙ የወታደራዊ፣ የሲቪልና የንግድ ተጠቃሚዎች አንድ ተፈላጊ አካል የሚገኝበትን ትክክለኛ ቦታ በመጠቆም ከፍተኛ ግልጋሎት ይሰጣል፡፡ በተለይም ዘመናዊው የአየር ትራፊክ አገልግሎት በዚህ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ቀልጣፋና አስተማማኝ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ ለውጊያ የሚሰማሩ የጦር ጀቶችም ሆኑ ርቀት ካለው ቦታ የሚተኮሱ ሚሳኤሎች ኢላማቸውን የሚያስተካክሉት በዚሁ በመጠቀም ነው፡፡ የጂፒኤስ አገልግሎት የአሜሪካ ሰራሽ ሲሆን ሩሲያኖችም የራሳቸው **ግሎናስ** (GLONASS - GLObal NAvigation Satellite System) የሚባል እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ለወታደራዊ አገልግሎት ብቻ የሚውል (ከዛሬ አምስት ዓመት ጀምሮ ለሕዝብ ነጻ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል) አላቸው፡፡ ቻይናውያኑም ኮምፓስ ናቪጌሽን (Compass navigation) እንዲሁም ሕንዶች (Indian Regional Navigational Satellite System) በሚባል በየራሳቸው የሳተላይት አገልግሎቶች ይጠቀማሉ፡፡ ከሁሉም በሚበልጥ መልኩ በ20 ቢሊዮን ኢሮ እየተገነባ ያለው የአውሮጳ ማኅበር የሚያሰራውና በጣሊያናዊው የስነፈለክ ተመራማሪ የተሰየመው **የጋሊሊዮ የሳተላይት ናቪጌሽን አገልግሎት** ነው፡፡ በሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ ሁለት የኦፐሬሽን ማዕከሎች፣ አንዱ በሙኒክ ጀርመን ሌላኛው ደግሞ በፉቺኖ ጣሊያን፣ ሲኖሩት ባለፈው የአውሮጳውያን ዓመት የመጀመሪያዎቹን ሁለት የሙከራ ሳተላይቶች አምጥቋል፡፡ ቀጣዮቹ ሁለት ደግሞ በያዝነው ዓመት ይመጥቃሉ፡፡ ይህ የሙከራ ሥራ በተሳካ ሁኔታ እንደተጠናቀቀ ተጨማሪ ሳተላይቶች የሚላኩ ሲሆን በ2019 (እአአ) የሳተላይቶቹ ቁጥር 30 እንደሚደርስ ይጠበቃል፡፡ ከዚህም ሌላ የጋሊሊዮ አገልግሎት ነጻ እንደሚሆንና ጂፒኤስና ሌሎቹ ከሚሰጡት አገልግሎት በጥራቱና አስተማማኝነቱ በጣም የረቀቀና የላቀ እንደሆነ ባለሙያዎች ይናገራሉ፡፡

ቆይቷል፡፡ የደኅንነት መዋቅሩ ይህንኑ ተረድቶ በገመድ አልባ ስልክ ኢንተርኔት መጠቀም እንዳይቻል አድርጓል፡፡ ምክንያቱም ገመድ አልባ መደበኛ ስልክ ለጊዜው ከደኅንነት መስተጋብር (ኔትወርክ) ጋር ባለመገናኘቱ ነው፡፡ ኢሜልና ፌስ ቡክ የኢንሳ ሰላዮች እንደፈለጉ የሚፈነጩበት ሲሆን በፌስ ቡክ በኩል የሚተላለፉ መልዕክቶችን አገር ቤት እንዳይደርሱ በፈለጉት ሰው አካውንት ውስጥ ገብተው ያጠፉታል፤ ይሰርዙታል።

አሜሪካ በምስራቅ አፍሪቃ አሸባሪነትን ለመቋቋም በሚል ህወሃትን ያስታጠቀችው ዘመናዊ የስለላ መሳሪያ ንጹሃን እንየታደኑበት እንደሆነ የሚገልጸው መረጃ ቃላቶች፣ ሃረጎችና ስሞች ኮድ ተደርገው በመረጃው ቋት (ዳታ ቤዝ) ውስጥ ይታሰራሉ። ከታሰሩት ቃላቶች ውስጥ አንዷ በድንገት ከአንድ ሰው አንደበት ስትወጣ ኔትወርኩ በቀጥታ “ኮዱ ተጠርቷል” በማለት ያሳብቃል። በዚያ መረጃ መሰረት ያቺን ቃል፣ ሃረግ ወይም ስም የተጠቀሙ ሰዎች ወዲያውኑ የክትትል ዝርዝር ሊስት ውስጥ ይገባሉ። ከዚያም ይሰለላሉ፤ ይበረበራሉ። የመረጃው ምንጮች ፖለቲከኞች በተመሳሳይ ኮድና በሚታወቀው የመለያ ስማቸው እየተጠራሩ ሲነጋገሩ አንዳንዴ የደኅንነት ሠራተኞቹ ራሳቸው “ሰዎቹ ምን ነካቸው?” እስከማለት የሚገረሙበት ወቅት እንደነበር ተናግረዋል።

7. ስለላ፡- በመያዶች፣ ኤምባሲዎችና ታዋቂ ተቋማት ላይ

ስለ ኢንሳ ከደረሱን መልእክቶች መካከል በመያዶች (መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች)፣ በኤምባሲዎች፣ በዲፕሎማቶችና ታዋቂ ተቋማት ላይ የሚካሄደውን ስለላ ያካትታል። መረጃው በስም ጠቅሶ እንዳብራራው የክርስቲያን ዕርዳታና ልማት ማኅበር (ሲአርዲኤ) - **Christian Relief and Development Association (CRDA)**፣ አክሽን ኤይድ በኢትዮጵያ **(ActionAid Ethiopia)**፣ ዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል፣ የሉተራን ዓለምአቀፍ ፌዴሬሽን **(LWF)**፣ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች፣ የተለያዩ ርዳታ ሰጪ ተቋማትና ሃላፊዎቻቸው እንዲሁም ዲፕሎማቶች

የሚጠቀሙባቸው የመገናኛ ዘዴዎች ከሚጠለፉት ወይም በስለላ መረብ ውስጥ ገብተው ከሚሰለሉት መካከል ጥቂቶቹ ናቸው።

ስዕል12. ከሚሰለሉ ድርጅቶች በጥቂቱ

የመገናኛ ዘዴዎቻቸውን በመጠቀም ከሚያደርጉት የስለላ ተግባር በተጨማሪ ኢንሳ ያሰለጠናቸው የተለያዩ ኤክስፐርቶችና ባለሙያዎች በሚጠረጠሩ ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥረው እንዲሠሩ አስፈላጊው ሁሉ ይደረጋል። የደኅንነት መዋቅሩ በሚፈልገው ድርጅት ውስጥ ሰራተኛ በማስመሰል ሰላይ አስርጎ ማስገባት ካልቻለ አስገዳጅ ቅድመ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ ከድርጅቱ ጋር ድርድር እንዲካሄድ ያደርጋል። በምሳሌ ከተጠቀሱ አንኳር ድርጅቶች መካከል ለምሳሌ ያህል ሲአርዲኤና የደኅንነት ጥናት ተቋም (አይኤስኤስ) **Institute for Security Studies (ISS)** በመባል የሚታወቅ የደቡብ አፍሪቃ ተቋም ተጠቃሽ ይሆናሉ።

በተለምዶ የመያዶች ህግ የሚባለው አዋጅ (የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራት አዋጅ) ቁጥር 621/2001ዓም ከመውጣቱ በፊት ሲአርዲኤ በመረጃ ሰዎች ቁጥጥር ሥር የነበረ ቢሆንም የደኅንነት ኃላፊዎች ሲአርዲኤ ውስጥ የራሳቸውን

ሰላዮች የድርጅቱ ተቀጣሪ ሠራተኛ በማስመሰል አስርገው አስገብተው ነበር። ለተቀጠሩት ሰዎች የተሰጠው መመሪያ የትምህርትና የሥራ ልምድ ማስረጃቸውን በሥራ ፈላጊነት ሰበብ እንዲያስገቡ፤ ከዚያም ለሥራ ወዲያው እንደሚጠሩና የታዘዙትን እንዲገብሩ ነበር። በዚሁ መሰረት የሲአርዲኤን የገንዘብ አጠቃቀም፣ የኃላፊዎችን የፖለቲካ አመለካከት፣ የሚደግፉትን ወይም የሚቃወሙትን የፖለቲካ መስመር እንዲሁም በድርጅቱ ውስጥ ሲሰሩ የነበሩና በሥራ ከተቃዋሚም ሆነ ከተለያዩ ዲፕሎማቶች ጋር ግንኙነት ያላቸውን የውጭ አገር ሰዎች ጓደኛ በማድረግና በስራ ሰበብ ማንነታቸውን መሰለልና ሪፖርት ማቅረብ ነበር። አክሽን ኤይድና ዓለም አቀፍ ቀይ መስቀልን በመሳሰሉ ድርጅቶች ውስጥም ተመሳሳይ ተግባር የተከናወነ ሲሆን በደቡብ አፍሪካው ድርጅት ላይ የተደረገው ደግሞ የተለየ ነው።

ከላይ ስሙ የተጠቀሰው የደቡብ አፍሪካ ተቋም (አይኤስኤስ) ላይ የተካሄደው ስለላ ብዙ መረጃ ማግኘት ባለማስቻሉ የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ አስገዳጅ ሁኔታን ፈጥሮ ነበር። መረጃው እንደሚያስረዳው በሙስና፣ በሰብዓዊ መብት፣ በመልካም አስተዳደር፣ በግጭት ትንተናና አወጋገድ፣ በሰላም ማስጠበቅ፣ በገንዘብ ከአገር ውጪ ማሸሽና በመሳሰሉት ጉዳዮች ዙሪያ ለአፍሪካ ህብረትና ለተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት በየወሩ ሪፖርት የሚያቀርበውና ጥናት የሚያዘጋጀው የዚህ ተቋም አካሄድ አስፈሪ የሆነባቸው የህወሃት ሰዎች የተቋሙ የኢትዮጵያ ፕሮግራም ዳይሬክተር በመሆን ሲያገለግሉ የነበሩት ግለሰብ ባለመታመናቸው ህወሃት/ኢህአዴግ የሚመድባቸውን ሰው ተቋሙ (አይኤስኤስ) ተቀብሎ ካልቀጠረ ጽ/ቤታቸውን ከአዲስ አበባ እንዲያነሱ ያስገድዷቸዋል።

በዚሁ አስገዳጅ ውሳኔ መሰረት የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ ከሆነችው አዲስ አበባ ቢሮአቸውን መልቀቅ ችግር የሆነባቸው የተቋሙ ኃላፊዎች እስከ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢደርሱም የተሰጣቸው መልስ የተባሉትን ማከናወን ብቻ እንደሆነ ተገልጸላቸው አቶ መሃሪ ታደለ ማሩ[10] የተባሉ የህወሃት ሰው የፕሮግራም ዳይሬክተር ለማድረግ ፈቅደው አዲስ አበባን ሳይለቁ ሥራቸውን እንዲቀጥሉ ተስማሙ።

[10] http://www.iss.co.za/show_personnel.php?office=4

ስዕል13. መሃሪ ታደለ ማሩ[xix]

አቶ መሃሪ[11] ገና ከጅምሩ የህወሃት አባል የነበሩ ሲሆኑ ቀደም ሲል በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተሃድሶ መርሃግብር ዳይሬክተር፣ በአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን ውስጥም በሕግ ባለሙያነትና በጎብረቱ የስደተኞች መርሃግብር ማስተባበሪያ ኃላፊ ሆነው አገልግለዋል። እንዲሁም (AU.COMMIT Campaign to Combat Trafficking in Human Beings) በመባል የሚታወቀውን የሰው ልጆችን በሕገወጥ መንገድ ወደተለያዩ አገራት ማስተላለፍ የሚዋጋውን የአፍሪካ ጎብረት መርሃግብር በመቅረጽና ተግባራዊ በማድረግ ሠርተዋል። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እስከ አፍሪካ ጎብረት በተለያዩ ደረጃዎች የህወሃት/ኢህአዴግን ዓላማ ሲያስፈጽሙ የቆዩ ግለሰብ በዲፕሎማሲ ሽፋን "አብረን መስራት የምንችልበትን ሁኔታ አመቻቹ" በተባለው መሰረት አይኤስኤስ አቶ መሃሪ ታደለ ማሩን በተቋሙ ውስጥ የግጭት መከላከያ ፕሮግራም ዳይሬክተር አድርጎ ለመቀበል ተገድዷል። ይህም በመሆኑ ተቋሙ በዴሞክራሲ መጓደል፣ በሰብዓዊ መብት ጥሰትና በመሳሰሉት ተግባራቱ ህወሃት/ኢህአዴግን በተመለከተ የሚያቀርበው ሪፖርትና ጥናት ለመገደብ ችሏል፤ ታንቋል።

ከስለላው በተጨማሪ በአስገዳጅ ሁኔታ የሚከናወኑ በርካታ ጉዳዮች አሉ። በመረጃው ትንታኔ መሰረት በሰብዓዊነት ስራ የተሰማሩ ድርጅቶች፣ ኃላፊዎች፣ የዕርዳታ ድርጅቶችና ሲቪክ ተቋማት ከስለላ መረብ ነጻ የሆኑበት ጊዜ የለም። መጨረሻ ላይ በህግ መስራት እንዳይችሉ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የህግ አማካሪና

[11] http://www.arpdafrica.org/index.php?option=com_contact&view=contact&id=1&Itemid=19

ተጨማሪ የህግ ባለሙያዎች የተዘጋጀው ህግ እንዲጸድቅ የተደረገው ኢንሳ ባቀረበው የስለላ ሪፖርት መሰረት ነው። መረጃው ያሰመረበት ጉዳይ ቢኖር የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ ሙሉ በሙሉ አፈና ላይ የተመረኮዘና አፈናውን የሚያጠናክሩ ተቋማትን በማደራጀት የሚፈጽመው የሰብዓዊ መብት ረገጣ፣ የንብረት ዝርፊያ፣ እስር፣ ግድያ፣ ግርፊያና ዕርዳታን ለፖለቲካ ተግባር የማዋለ ተግባር እንዳይታወቅበት ስለሚፈራ የመያድ ህግ ለማዘጋጀት መገደዱን ነው።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በከፍተኛ ቴክኖሎጂ ከሚደገፉት እጅግ ጥቂት ኤምባሲዎች በስተቀር አብዛኞቹ ኤምባሲዎች፣ ታዋቂ ተቋማትና በሰብዓዊ ስራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች፣ ታዋቂ ዲፕሎማቶችና የመሳሰሉት በደኅንነት መረብ ስር ተይዘው ሲሰለሉና ሲበረበሩ የሚውሉ ናቸው። ታላላቅ ሆቴሎች[12] ውስጥ የሚከናወኑ ስብሰባዎችና በግል ደረጃ የሚካሄዱ ውይይቶች ሁሉ ተለቅመው የመረጃ መረቡ ውስጥ እንዲካተቱ እንደሚደረግ ለአገዛዙ ቅርበት ያላቸውን ሆቴሎች በመዘርዘር መረጃው ይተነትናል። በተለይ በአንድ ትልቅ ሆቴል ውስጥ ግለሰቦችንና ታዋቂ ሰዎችን በመከታተል መረጃ የመሰብሰብ፣ በግል (በምስጢር) የሚደረጉ መዝናኛዎች ሳይቀሩ እየተቀረጹ ለፖለቲካ ስራ ማስፈራሪያነት እንደሚውሉ የሚያስረዳው መረጃው በሁለት ሆቴሎች ውስጥ በስውር የድምጽ፣ የስዕልና የቪዲዮ መረጃ የሚሰበስቡትን የውጪ አገር ዜጎች ማንነት፣ ክፍያ የሚያከናውኑላቸውን ክፍሎች፣ ከነመኖሪያቸው ይፋ አድርጓል። ሰዎቹ የቅንጅት ፖለቲካ በተፋፋመበት ወቅት ከአረብ አገራት ተቀጥረው እንደመጡና አሁን ድረስ የመረጃ ሰራተኛነታቸውን እያከናወኑ እንደሆነ ያጋልጣል። እነዚህ ክፍሎች የሚታወቁት በውስን ባለስልጣናትና ባለሃብቶች እንደሆነም ለማወቅ ተችሏል።

የጋራ ንቅናቄያችን እምነት እነዚህን በዚህ እርኩስ ተግባር ላይ የተሰማሩ ዜጎች ቁምር ነጻ የሚወጡበትና እንደማንኛውም ዜጋ ሳይሰለሉ ያመኑበትን

[12] በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች የሚገኙ ታላላቅ ሆቴሎች የተቋቋሙት ለህወሃት/ኢህአዴግ ቅርበት ባላቸው ግለሰቦች ወይም የህወሃትን ዓላማ በግልጽ በሚያራምዱ ሰዎች እንደሆነ ይታወቃል። ሆቴሎቹ እንደ መዝናኛ ቦታ ለንግድ የተከፈቱ ቢሆንም ከበስተጀርባው ግን የሚያካሂዱት ከፍተኛ የሆነ የስለላ ሥራ እንዳለ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በሰለጠነው ዓለም እንደዚህ ዓይነቱ አሳፋሪ ተግባር የሰውን ነጻነትና ክብርን የሚጋፋ፣ የሚያስወነጅልና የሚያስፈርድ ቢሆንም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች ይህንን ለማድረግ የማይታሰብ መሆኑ ግልጽ ነው። ከአገዛዙ ጋር ምንም ዓይነት ንክኪ በሌላቸው ግለሰቦች የተከፈቱ ሆቴሎችም ቢሆኑ አንዳንድ ተጠርጣሪ ሰዎች የሚያዘወትሩባቸው ከሆኑ ይህንን መሰሉን የስለላ ተግባር ሆቴሎቹ እንዲፈጽሙ በህወሃት መገደዳቸው የማይቀር ነው። ዓላማው የሰዎችን እጅግ ምስጢራዊና የግል የሆኑ ጉዳዮችን በማስረጃ በመያዝ ከትግልና ከፖለቲካ ማራቅ በመሆኑ እንደ ኢትዮጵያ ዓይነት በገሃድ ወጥቶ "**ጥፋት ሰርቻለሁ፤ ይህ ግን ከቆምኩለት የትግል ዓላማ ሊያስወጣኝ አይገባም**" በማለት ሕዝብን በግልጽ ይቅርታ መጠየቅ ባልተለመደበት ጎብረተሰብ ውስጥ ይህ ዓይነቱ የህወሃት እኩይ ዓላማ በርካታዎችን ከትግል ሜዳ ፎጣ ወርውረው እንዲወጡ ወይም ከአገር እንዲሰደዱ አድርጓቸዋል፣ እያደረጋቸውም ይገኛል።

የፖለቲካ ድርጅትና ተቋም የሚደግፉበትን ስርዓት ይፈጠር ዘንድ በመሆኑ ያገኘውን መረጃው ሙሉ በሙሉ ባናወጣም ባለስልጣኖች እንዴት እንደሚሰለፉ፣ ባለሃብት የሚባሉ የህወሃት/ኢህአዴግ አገልጋዮች እንዴት የመረጃ መዋቅሩን እንደሚያግዙ፣ ምን ያህል የመስመር ሰላዮች አዲስ አበባን እንደሚሰልሉ፣ በመከላከያ የሎጂስቲክ መምሪያ የሚካሄደውን ሙስና ስለምትመራዋ እንስት፣ "ጎንደሬ ነን" ስለሚሉት ሰላዮች፣ የደህንነት አባላትና ባለስልጣናት ሆን ተብሎ ሙስና ውስጥ እንዲዘፈቁ ስለሚደረግበት ስልትና የታላላቅ ሆቴሎችና የስለላ ትስስር ተከታታይ ጽሁፍ እናስነብባለን።

8. የፖለቲካ ፓርቲዎች ስብሰባ ምሥጢር ነውን?

ተቃዋሚ ፓርቲዎች የሚያካሂዱት ስብሰባ ምሥጢር ስለመሆኑ ማረጋገጫ የለም። አብዛኛውን ጊዜ "ምሥጢራችን ይፋ ሆነ" በሚል ፓርቲዎች እርስ በርስ ሲካሰሱና ሲወነጃጀሉ ይሰማል። ከዚህም በላይ የሚከፋፈሉበትና ደጋፊዎቻቸው ሳይቀር ተስፋ የሚቆርጡበት ሁኔታ ይስተዋላል። አንዳንድ ዓላማ የለሾችና ጥቅመኛ "ምስለኔ" ፖለቲከኞች ወደ ፖለቲካ ድርጅቶች ሰርገው ቢገቡም የፓርቲዎች ምሥጢር የሚባክንበት ሌላው መንገድ በስለላ በሚገኝ መረጃ እንደሆነ ከኢንሳ የወጡ መረጃዎች ያመለክታሉ። ነገሩ እንዲህ ነው።

በህገ መንግሥቱ መሰረት ፈቃድ ጠይቀው በስብሰባ ቦታ ወይም በራሳቸው ቢሮ ተቃዋሚዎች፣ የሲቪክ ተቋማት፣ ዲፕሎማቶች፣ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች፣ የቤተክርስቲያን አመራሮችና ሌሎች ተፈላጊዎች ስብሰባ ሲቀመጡ ከርቀት (ከ200 እስከ 300 ሜትር የሚሆን) መኪና ውስጥ በመሆን የስለላ ሰዎች ይቀርጹታል። ይህንኑ ለማከናወን ከርቀት የሚያዳምጥ መሣሪያ (ሪሞት ሊስኒንግ)፣ ከርቀት የሚቀርጽ መሣሪያ (ሪሞት ሪኮርድ ዲቫይስ)፣ ከርቀት የመስሚያና ማስተጋቢያ መሣሪያ (ሪሞት ስፒከር) ወዘተ ይጠቀማሉ።

በዚህ ዓይነት መልኩ ስለላ በማካሄድ የተቀረጹ ድምጾች እየተቆረጡ ከተቀጠሉ በኋላ ለማስፈራሪያነት፣ ለክስ ማስደገፊያነት፣ ለተጨማሪና ለህጋዊ መረጃ

መቀበያነት፣ አፋኝ ህግ ቀድሞ ለማውጣት፣ በእጃቸው በያዙት መገናኛዎች እንዲሁም በተቀላቢ ጋዜጦችና በኤፍኤም ራዲዮኖች ለቅስቀሳ ይጠቀሙበታል። የመረጃው አካላት ይህንኑ እውነት ሲያጠናክሩ በቅርቡ አቶ መለስ "ለማይናገረውና የግላቸው ለሆነው" ምክር ቤት "አሸባሪ" ብለው የወነጀሏቸውን ኢትዮጵያዊያንን በተመለከተ "ማስረጃ አለን" እያሉ ስርዓት ለቀው የተናገሩትን ማሳያ ያደርጋሉ።

ወደኋላ መለስ ብለን የተከሰተውን ብንመለከት፡- በሱናሚ ማዕበል የተሰየመው የቅንጅት መግነንና በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት ያሳሰበው የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ የስለላ መረብ በወቅቱ ከፍተኛ መረጃ የሚሰበስበው ከቴሌ ነበር። የቅንጅት አመራሮችን፣ ተባባሪዎችንና ዋና ደጋፊዎችን ስልክ በመጥለፍ ድምፃቸው እንዲቀረፅ ይደረጋል። በወቅቱ የሞባይል ዲዚሾን ውስጥ ባለው መምሪያ የደኅንነቱ ኃይሎች ክፉኛ እጃቸውን ከትተው የተተነፈሰውን ሲለቅሙ ድርጊቱ ያስቆጣቸው ባለሙያዎች ነበሩ። በተለይም ሥራውን እንዲሰሩ የታዘዙት ወገኖች የቅንጅት አመራሮች የሞባይል ስልካቸውን ሲጠቀሙ ፍፁም ጥንቃቄ አለማድረጋቸው በእጅጉ ያሳዝናቸው ነበር። በአንድ የአፍሪካ አገር የቴሌኮም ኩባንያ ውስጥ በከፍተኛ ኃላፊነት የሚያገለግሉና፣ በቀድሞ በብሮድ ባንድ ዲቪዥን ውስጥ ሲሰሩ ቆይተው የተሰደዱ ባለሙያ እንደሚመሰክሩት ወቅቱ "አስቸጋሪ" ነበር።

የቅንጅት ሰዎች የሚለዋወጡትን መረጃ ለህወሃት/ኢህአዴግ የሚያቀብለው ቴሌ አስከሬን የታሳረበት ቤት ይመስላቸው እንደነበር የሚገልፁት የቴሌ ባለሙያዎች በተዘዋዋሪ እዚያው ቴሌ ውስጥ ሌላ ዲቪዥን በሚሰሩ ባልደረቦቻቸው አማካይነት መረጃውን ለቅንጅት ሰዎች ማድረሳቸው ሲታወቅ ከስራ ታግደዋል፣ ታስረዋል፣ ... መረጃውን ከሰጡ በኋላም ራሳቸውን ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ያሸሹ ጥቂት አይደሉም። ራሱ አገዛዙም "ዓይናችሁን ላፈር" በማለት ከሥራ ያስወገዳቸው በርካታዎች ናቸው። ይህ ልምድ ከተወሰደ በኋላ ነው እንግዲህ ቴሌ ሙሉ በሙሉ ወደ አፈና ተቋምነት እንዲሸጋገር ሌት ተቀን መሠራት የተጀመረው። በታማኝ ኃይሎች እንዲደራጅ ተደርጎ ኢትዮጵያዊ እምነትና ፍቅር ያላቸው እንዲራገፉ የተወሰነው። ከዚህ በኋላ ነው የምዕራብ ቴሌኮም ኩባንያዎች "በቃችሁ" የተባሉት።

በአገዛዙ በኩል እንዲህ ያለው መስመር የለቀቀ ተግባር ሲከናወን የፖለቲካ ፓርቲዎች በበኩላቸው ደግሞ እንዲህ ያለውን ህገወጥ ተግባር በተደጋጋሚ

ማውገዝና መቃወም ሲገባቸው ዝም ማለታቸው ለስለላው ሰዎች ድፍረት መስጠቱን የመረጃው ምንጮች ይናገራሉ። የኢንሳ ሰዎች እንደሚሉት የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ከተቃውሞ ባለፈ መልኩም ለደህንነቱ የተሳሳተ መረጃ እንዲደርስ በማድረግ ስለላውን ግራ ማጋባት አለባቸው። አንዳንዴም ሆነ ብለው ለደኅንነቱ እንዲደርስ የሚያደርጉትን መረጃ ለዓለም አቀፍ የሰብአዊ ተቋማት፣ ለተለያዩ አቅም ያላቸው መንግስታትና መገናኛዎች አስቀድመው በማድረስ የህወሃት/አህአዴግ አገዛዝ የአፈና መዋቅር መረጃውን ለውንጀላና ለክስ ሲጠቀምበት ጠብቆ በአለም አቀፍ መድረክ እርቃኑን ማስቀረት የሚያስችል ስራ መስራት ይቻላል። በየጊዜው አዳዲስ ኮዶችን ለደህንነቱ እንዲደርስ በማድረግ የመረጃው ኮሮጆውን ማወዛገብና ማሳከርም ቀላል ሥራ እንደሆነ ይናገራሉ። እንዲህ ዓይነት እዚህ በዝርዝር ልንጠቅሳቸው የማንችላቸውን በርካታ ተግባራትን በመፈጸም ስለላውን መልሶ ማወናበድና መልሶ መሰለል ሲቻል በየጊዜው በሚደረጉ ጥንቃቄ አልባ ድርጊቶች የስለላውን መረብ ረቂቅና ሊደረስበት የማይቻል አድርጎ የማሰብ ሁኔታ በጎብረተሰባችን ዘንድ ይስተዋላል።

ባለሙያዎቹም አበክረው የተናገሩት ቁም ነገርና ከኢንሳ የወጣው መረጃ የተጣጣሙበት ጉዳይ ቢኖር የፖለቲካ ፓርቲዎች ስብሰባቸውን አውላላ ሜዳ ላይ በማከናወን ይህንን ያደረጉበትን ምክንያት ለዓለም አቀፍ የሚዲያ ተቋማት፣ ተጽዕኖ ፈጣሪ ለሆኑ ድርጅቶችና አገራት በምስል በማስደገፍ ማሳወቅ ነው። እንዲህ ያለው ስለላውን የሚያጋልጡ ድርጊቶች ሲደጋገሙ በአዲስ አበባ የሚቀመጡ ዲፕሎማቶችና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጉዳዩን ለራሳቸው ሲሉ አጀንዳ ያደርጉታል። በራሳቸው ላይ የሚካሄደውን መለስ ብለው እንደቃኙም ይጠቁማቸዋል። ከዚህም በተጨማሪ ህዝቡ ስርዓቱን በአግባቡ ተረድቶ ካፈና ለመገላገል የሚያደርገውን ትግል ያነቃቃዋል።

በየዘርፉ ተለያይቶ የቀረበው የኢንሳ ሰዎች ማስረጃ ህወሃት/ኢህአዴግ በተመሳሳይ ሁኔታ የሰበሰበውን ህገወጥ ማስረጃዎች በባለሥልጣናት፣ በባለሥልጣናት ሚስቶች፣ በጠባቂ አንጋቾች፣ በቢሮ ጸሃፊዎች፣ በባለሃብቶችና በቅርብ ሰዎች፣ አንዳንዴም ቅምጥ በመላክ አሳዛኝና አጸያፊ የተባለውን የስለላ መዋቅርና አሰራር ይዘረዝራል። የዚህ ጽሁፍ ዋና ርእስ ከቴሌኮም ጋር በተያያዘ አገዛዙ የግለሰቦችን

መብት በሚጥስ መልኩ እያካሄደ ያለውን አፈናና ስለላ ማጋለጥ በመሆኑ ዝርዝሩን በሌላ ጊዜ እንመለስበታለን።

9. የመረጃ ጫካ ውስጥ ግቡ!!

የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ የኢትዮጵያን የቴሌኮም አገልግሎት በአንድ ተቋም ስር በማድረግ የምዕራቡን አገራት የቴሌኮም ኩባንያዎችን ሲያባርር ውጥኑ አንድ ብቻ ነበር። አሁን በቻይናው ቴሌኮም ኩባንያ ተገንብቶ ለአፈና የዋለውን ቴሌን ሙሉ በሙሉ መቆጣጠር። የተለያዩ አገልግሎት አቅራቢዎች የቴሌኮም ኩባንያዎች ካሉና የተለያዩ መልዕክት ማስገቢያ በሮች (gateway) ስራ ላይ ከዋሉ የስለላው ተቋም በዜጎች የግል ጉዳይ ውስጥ ሳይቀር እንደፈለገ የመፈንጨት አቅም ያጣል። እንደፈለጉ ኢሜል (ጸዳቤ) እና ስልኮችን መጥለፍ አስቸጋሪ ይሆናል። ኩባንያዎቹ ለእንዲህ አይነቱ የአፈና ተግባር ስለማይስማሙና ዓለም አቀፍ መስፈርት ያላቸውን መጠይቆች ስለሚያቀርቡ ስለላውን ሙት ያደርገዋል።

“እንደ አንድ የቴሌኮም ባለሙያ የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ የቻይናውን የቴሌኮም ኩባንያ ባስገባ ጥቂት ጊዜ የምዕራቡ ዓለም የቴሌኮም ኩባንያዎች የተከሏቸውን አንቴናዎች ነቃቀሎ መጣል የእብደት ያህል ይሆንብኛል። የወደመውን የአገር ሃብት ሳስበው አገሪቱ ወዴት እያመራች እንደሆነ ያሳየኛል” ሲሉ ሃዘን የተቀላቀለበት አስተያየት የሰጡት ባለሙያ “ሃያ ዓመት የአገር ሃብት የፈሰሰበትን ቴክኖሎጂ ሃብታም አገሮች እንኳን አያወድሙትም። አሮጌውንና አዲሱን አቀላቅለው ይጠቀሙበታል” በማለት ገልጸዋል። በአንድ ወቅት አገር ውስጥ ያሉ ባለሙያ ድርጊቱን “ክህደት” ካሉት በኋላ የምዕራብ አገሮችን ቸልተኛነት ወቅሰው ነበር። ለዚህም ነው ምዕራባዊያኑ የአፈና ስርዓት ከመደገፍ ይልቅ ኢትዮጵያ ላይ ያላቸውን አቋም እንዲመረምሩ የሚወተውቱት።

አሁን ባለው ቴክኖሎጂ ወደፊት አገርና ህዝብ ዕዳ ላይ ከመውደቅ ውጪ ሌላ አማራጭ እንደሌለ ባለሙያው ጠቁመዋል። ይህ ሁሉ አልበቃ ብሎ “አገሪቱ ከዘረጋችው ቴክኖሎጂ ጋር የሚስማማ የሞባይል ቀፎ በሚል ዜጎች እየተታለሉ

ሰላይ ቤታቸው ይዘው እንዲገቡ ይደረጋል”[13] በማለት የማስጠንቀቂያ መልእክት ያስተላልፋሉ። ጉዳዩ አገራዊ አጀንዳ ሊሆን እንደሚገባውም ያሳስባሉ።

ቴሌን የሚቆጣጠረው ህወሃት/ኢህአዴግ ብቸኛ የአገሪቱ የመረጃ አገልግሎት አቅራቢ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ወደ አገር ቤት የሚገቡ መረጃዎች በቴሌ የመግቢያ በር (gateway) አማካይነት የሚያስተናግድ ስለሆነ ከቻይና በታጠቀው ቴክኖሎጂ አማካይነት የመግቢያ በሩ ላይ የሚጠረጠሩ የኮምፒውተር፣ የሰው ስሞች፣ አንዳንድ ቁልፍ ቃላቶች ራውተሩ (router) ላይ እየታሰረ በቀጥታ ኢንሳን ለሚመግበው የደህንነትና የስለላ መስተጋብር (ኔት ወርክ) ያሻግራል። **እንግዲህ ህወሃት/ኢህአዴግ ቴሌን ከምዕራባውያን የቴሌኮም ኩባንያዎች ነጥቆ በአዲስ መልክ ያደራጀበት ዋና መነሻ ይህና ይህ ብቻ ነው። ስለላ!! እየሆነ ያለውም ይኸው ነው!! ይህም ቢሆን ግን ሙሉ በሙሉ ሊባል የሚችል ቀርቶ አምስት በመቶ የሚሆን የስለላ መዋቅር እንኳን መዘርጋት እንዳልቻለ ባለሙያው ያብራራሉ።**

በቀን ውስጥ ወደ አገር ቤት የሚገቡና ከአገር ቤት የሚወጡ የኢሜል (የጸዳቤ)፣ የአጭር መልዕክት (SMS) እና የስልክ መልዕክቶች በሚሊዮን የሚቆጠሩ ናቸው። ህወሃት/ኢህአዴግ እነዚህን ሁሉ መልዕክቶች ሊሰበስባቸው፣ ሊመረምራቸውና ሊተነትናቸው ከቶውንም አይችልም። አቅሙም፤ ብቃቱም የለውም። የቴክኖሎጂው ባለቤት የሆነችው ቻይና እንኳን አታስበውም።

የህወሃት የደህንነት መዋቅር የቁጥጥር ስራውን ለመስራት በ40ና 50 ሺህዎች የሚጠጋ የሰለጠነ ልዩ የመረጃ ፖሊስ ኃይል ማደራጀት ያስፈልገዋል። በየቀኑ ወደ አገር ቤት የሚገባውን የመረጃ መጠን ለመቆጣጠርና ለማገላበጥ የማይቻልበት ሌላው ዓብይ ጉዳይ ተጠቃሚዎች “የመረጃ ጫካ” ውስጥ ሲደበቁ ነው። ወይም ከፍተኛ ትራፊክ በሚኖርበት አካባቢ እይታ ውስጥ ባልገቡ ኮምፒውተሮች መገልገል ሲችሉ ነው። ይህ ዋንኛ ነገር ግን ትንሹ የጥንቃቄ አይነት ነው። (ዝርዝር ሃሳብ በሚቀጥለው ክፍል 10 ተጠቅሷል)

ከቀላል ጥንቃቄ ጉድለት የሚደርሱትን አደጋዎች መከላከል ባለመቻሉ ብዙውን ጊዜ ሰዎች ራሳቸው ምስጢራቸውን ለስለላ መዋቅሩ ያቀብላሉ። በስለላው

[13] ማኔጅመንቱን ለፊረንሳዩ የቴሌኮም ኩባንያ የሰጠው ኢትዮ ቴሌ ባለፉት ሁለት ዓመታት አገልግሎቱን በተቀላጠፈና በተሻሻለ መንገድ ያከናውናል ተብሎ ሲጠበቅ እየተከሰተ ያለው ነገር ቢኖር በአገልግሎት ደረጃ ምንም ያልተሻሻለ እንደሆነ እንዲያውም እንደባሰበት፣ በአገልግሎት ሽፋን ደረጃ ደግሞ የሚታይ ለውጥ ከማምጣት ይልቅ ያለፉትን ሁለት ዓመታት የሞባይል ስልክ ቀፎዎችን እንደ ችርቻሮ ነጋዴ ሲሸጥ መክረሙ ብዙዎችን ያነጋገረ ጉዳይ ቢሆንም ያለ ምክንያት የተደረገ ጉዳይ ግን እንዳልሆነ ይስተዋላል።

ድርጅት ክፋትና፣ በተጠቃሚዎች ሞኝነት ስለላውን የሚያቀሉና ራሳቸውንና ሌሎችን ለአደጋ የሚያጋለጡ ወገኖች ጥቂት አይሆኑም። ሆን ብለው የሚያወናብዱትን ጨምሮ፤ በቢሯቸው ኮምፒውተሮች፣ በራሳቸው የስልክ ሲም ካርዶች፣ በግል ላፕቶፖች፣ በግል ስም በተመዘገቡ አገልግሎቶች፣ ወዘተ መጠቀም በተለይ ከህወሃት/ኢህአዴግ ጋር ከሚደረገው ትግል አኳያ ፈጽሞ ሊታሰብ የማይገባው ስህተት እንደሆነ ባለሙያው ይመክራሉ። በግለሰቦች ስህተት የስለላውን ድርጅት የማግዘፍና ከጥንቃቄ ይልቅ ወደ ፍርሃቻ የማዘንበል ሁኔታ የሚስተዋለውም ለዚሁ ነው። ከባለሙያው ያገኘነውን መሰረታዊ የጥንቃቄ ምክር እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

10. “በስማችሁ በተመዘገበ ኮምፒውተር አትጠቀሙ”

ብዙውን ጊዜ በማይታወቁ የኢሜል (የጸዳቤ) አድራሻዎች ማስታወቂያ ወይም ግብጣ መሰል መልዕክቶችን በመላክ ተቀባዩ ሰው የተላከለትን መልዕክት ለማንበብ መልዕክቱን ሲከፍተው የኮምፒውተሩ አድራሻ ቁጥር (IP address) በቀላሉ መያዝ ይችላል። ይህንን ለመሸሽ እንዲህ ዓይነት መልዕክቶች በተለይም ከማይታወቅ ግለሰብ ወይም ድርጅት ሲመጡ ሙሉ በሙሉ አለመቀበል፡፡ መልዕክቱ አባሪ (attached) ሆኖ ከመጣም በፍጹም አለመክፈት እንዲያውም ወዲያውኑ ከመልዕክት ሣጥን ውስጥ መሰረዝ፡፡ በስማችን በተመዘገቡና በቀላሉ ስማችንን ከ(IP) አድራሻ ጋር ለማዛመድ በሚቀል ኮምፒውተሮች ላይ ምስጢር መላላክ የዋህነት ነው። በተለይም በፖለቲካ የሚጠረጠሩ ሰዎች በፍጹም ከእንዲህ ያለው የየዋህነት አጠቃቀም ሊታቀቡ ይገባል። በተለይም በዘመዶቻቸውና በሚቀርቧቸው ሰዎች ኮምፒውተሮች አለመገልገል በዋንኛነት ሊያስቡበት የሚገባ ተግባር እንደሆነ ይገባል። ከዚህ ይልቅ በሌሎች ህዝባዊ በሆኑና የማን እንደሆኑ በውል በማይለዩ ቢለዩም የተጠቃሚው ቁጥር እጅግ ከፍተኛ በሆነባቸው ኮምፒውተሮች መጠቀምን እንደ አማራጭ መውሰድ አለባቸው፡፡

በአገር ውስጥ የሚጠረጠሩ ወይም በመረጃ ሊስት ውስጥ የሚገቡ ኮምፒውተሮች ላይ የሚገለገሉ ሁሉ የምስጢርቃላት (password) በሚጽፉበት ጊዜ

የእያንዳንዱን ቃላት ድምጽ ስለሚሰማ የፊደልሰሌዳቸውን (keyboard) መደበቅ አለባቸው። ይህ ማለት የፊደልሰሌዳቸው አንድ ቃል በተነካ ቁጥር የተነካውን ፊደል ድምጽ በመቅረጽ የምስጢርቃላቸውን በቀላሉ በሰላዮች እጅ ሊወድቅ ስለሚችል የግያጊያቸውን አቀማመጥ (የኮምፒውተሩን settings) በመቀየር የፊደልሰሌዳው ሲመታ ድምጽ እንዳይኖረው ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል።

Start → Control Panel → Sounds, speech and audio → Sounds Tab → select your settings.

ከራስ ስምና ልዩ መለያ ጋር ግንኙነት የሌላቸው የኢሜል (የጸዳቤ) አድራሻ መጠቀም በቀላሉ ራስን የመከላከያ መንገድ ሲሆን፣ ቶሎ ቶሎ የምስጢርቃላትን (password) መቀያየር የስለላውን ስራ በየጊዜው አድካሚ ያደርገዋል። በተመሳሳይ የምስጢር ቃል ለረዥም ጊዜ መጠቀም ከቶውንም መታሰብ የለበትም - ተጠቃሚዎች በየሶስት ወይም በየስድስት ወሩ የምስጢርቃላቸውን (password) መቀየር መልመድ አለባቸው።

በአብዛኛው ወይም በብዛት አገልግሎት ላይ ያሉ ቃላቶች ሲኖሩ፣ በሌላ አነጋገር በመልዕክቶች ውስጥ የሚደጋገሙ ቁልፍ ቃላቶች ሲበዙ "እነዚህን ቃላት ካገኘህ ንገረን" በሚል የቴሌ ራውተር (router) እንዲያቃጥር ቃላቶቹ ይታሰሩለታል። እነዚህን ቃላቶች በተጠሩ ቁጥር መሣሪያው እየነጠለ እያወጣና እየሰበሰበ ለስለላና ለትንተና ይልካል። ቴሌና ኢንሳ ባላቸው የጋራ ድር ወይም የመረጃ መቀባበያ መረብ ተቀብለው ይተነትኑታል። ስለዚህ ጥርጣሬ ውስጥ የሚገቡ ቃላቶችን አብዝቶ አለመጠቀም ተመራጭ ይሆናል። ከታዋቂ ፖለቲከኞች ስምና የፓርቲ መለያዎች ጀምሮ። እነዚህን ቃላቶች መጠቀም አስፈላጊና የግድ ከሆነ ተተኪ ቃላቶችንና ስሞች ከመልዕክት አቀባዩ ወይም ተቀባዩ ጋር በመስማማት በኮድ መጠቀም። (ለምሳሌ ጨካኝና ነፍሰገዳይ የሆነውን ጋሽ መልካሙ፣ አቶ ሽጉጤ በማለት፣ በሙስና የተጨማለቀውን አቶ ደግሰው በማለት፣ ወዘተ)

በተመሳሳይ ግያጊ (ኮምፒውተር) አብዛኛውን ጊዜ የሚከፈቱ ድረገጾችና ፓልቶኮች ላይ ተጠምደው የሚውሉ ተላላኪዎች ስራቸው የኮምፒውተር አድራሻ (IP address) መልቀም ስለሆነ አታጋይ ፖለቲከኞች በስውር የሚጠቀሙበት ኮምፒውተር እንዲህ ያለውን ተግባር ከማከናወን መታቀብ አለባቸው። በተለይ

ጋዜጠኞችና ታዋቂ ፖለቲከኞች ከዚህ አይነት የኮምፒውተር አጠቃቀም መገታት ይኖርባቸዋል።

በቴሌ የመግቢያ በር የሚያልፉ መልዕክቶች ልክ ለትራፊክ ፖሊስ እንደሚተላለፍ የመኪና ታርጋ የግያጊዎች (ኮምፒውተሮች) አድራሻና ((IP address) የሲም ካርዶች ቁጥር የታሰረለት ወይም የተሰጠው ራውተር፣ መልዕክቱን ኮፒ በማድረግና በማጣራት (filter በማድረግ) ለስለላ ድርጅቱ የኢንሳ መረብ የሚመግብበት አወቃቀርና መስተጋብር ያለው የቴሌኮም መሳለጫ የመዘርጋቱ ምስጢር በከፍተኛ ደረጃ መከላከያ ቢኖረውም በዋናነት ግን በአገር ቤትና በውጭ አገር ያሉ የተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ የሲቪክ ማህበራትና ህጋዊ ተቋሞች ድርጊቱን በመቃወም ያለመሰልቸት ትግል ማድረግ ይገባቸዋል።

ታዋቂና የክትትል ሊስት ውስጥ ያሉ ፖለቲከኞች ወደ አገር ቤት ሲገቡ የተለያዩ አገሮችን ቢጠቀሙ ይመከራል። አንዱና ትልቁ (Virtual Private Network VPN) በመግዛት ወይም በመከራየት አገር እየቀያየሩ መልዕክት መላክ ሲሆን ሌላው ሁለት መልዕክት የሚቀያየሩ ሰዎች በጋራ ተመሳሳይ ክትብቁስ (ሶፍትዌር) በመጫን በኮድ የሚላከውን መልዕክታቸውን አስተማማኝ ማድረግ ይችላሉ። አንድ ሰው መልዕክት ሲልክ የተላከበት የጸዳቤ (የኢሜል) ወገም (አካውንት) መልዕክቱን ወደ ኮድ ቀይሮ እንደማይነበብ አድርጎ ለመልዕክቱ ተቀባይ ያደርሰዋል። እንዲሁም ባለሙያው እንደሚሉት ሁለት ሰዎች ተመሳሳይ ክትብቁሶች (ሶፍትዌሮች) በመጫን የተቀያየሩት ኮድ ወይም ቁልፍ መልዕክቱ decode አንዳይደረግ ይከለክላል። ይህ ሌላው ራስን ከስለላው መረብ የመጠበቂያ መንገድ ነው።

የVPN አገልግሎት ውድ ዋጋ የሚያስወጣ ባለመሆኑ የመግቢያ በር እየቀያየሩ መልዕክት መቀያየር ለታዋቂ ፖለቲከኞችና የፖለቲካ አመራሮች እጅግ ወሳኝ ይሆናል። በኬንያ፣ በደቡብ አፍሪካ፣ በአውስትራሊያ ወዘተ የመግቢያ በር በመቀያየር መጠቀም ማንኛውም ዓይነት መልዕክቶችን በአስተማማኝ መንገድ ማድረስና ከእይታ ውጪ ለመሆን ያስችላል።

በአጠቃላይ ጥንቃቄን በተመለከተ ከዚህ የሚከተሉትን ነጥቦች መከተል ከፍተኛ ጥቅም ያለው ሲሆን ከሁሉ በላይ ደግሞ ባለሙያዎችን ማነጋገርና የራስንም ጥረት በማድረግ ተጨማሪ ራስን የመከላከያ መንገዶችን መከተል ተገቢ ነው።

- ጠንከር ያሉ የምስጢርቃላት (password) መጠቀም፤ በተለይም እነዚህን የምስጢር ቃላት ከቁጥርና ከልዩ ምልክቶች (#, $, % … ዓይነቶች) የተውጣጣ ማድረግ፤
- የምስጢርቃልዎን ለሚጠይቅ ማንኛውንም ዓይነት ኢሜል (ጸዳቤ) መልስ አለመስጠት፤
    - አንዳንዶቹ ከ Yahoo፣ Googlemail or gmail . . . የተላከ አስመስለው “የመረጃ ቋታችንን (database) እያስተካከልን ስለሆነ የምስጢርቃልዎን (password)፣ የትውልድ ዘመን፣ ወዘተ ለማረጋገጫ ላኩ” የሚል መልዕክት በመላክ ጥያቄ የሚያቀርቡ ሲሆን በመልዕክቱ ላይም “ይህንን መረጃ የማትልኩ ከሆነ የኢሜይል ሣጥናችሁ ይዘጋል” የሚል ማስፈራሪያ እየሰጡ የሚያደርጉትን ሙከራ ማንም መቀበል የለበትም። እንደ Yahoo፣ Googlemail or gmail ያሉት የጸዳቤ (ኢሜይል) አቅራቢ ድርጅቶች የማንንም ሰው የምስጢርቃል ፈጽመው አይጠይቁም - በጭራሽ።
- በጸዳቤ (ኢሜይል) የሚላኩና ልብን የሚሰልቡ መልዕክቶችን (ሎተሪ አሸንፈዋል፣ ልዩ ሽልማት እየጠበቅዎ ነው፣ ወዘተ) በመላክ ከዚያው ጋር ይህንን ለመቀበል እዚህ ላይ ይጫኑ የሚል መልዕክት አክለው የሚልኩ የግለሰቦችን ምስጢር ለመበርበር በስውር የሚያስሩት መረጃ ጠቋሚ ከመልዕክቱ ጋር በመኖሩ በጭራሽ በእንደነዚህ ዓይነት የጸዳቤ (ኢሜይል) መልዕክቶችን ሳይታለሉ ወዲያውኑ ከመልዕክት ሳጥንዎ ይሰርዟቸው። ቢቻልም የኢሜይል መልዕክቱን አይክፈቱት።
- ከማያውቁት ግለሰብ ወይም ድርጅት የሚላክልዎትን የኢሜይል መልዕክት ቢቻል ሳይከፍቱ በቀጥታውኑ በመሰረዝ ወደ ማኅደረ ቁሻሻ (Trash folder) ይስደዱት። ከከፈቱትም ቶሎ አንብበው አላስፈላጊ መልዕክት መሆኑን ሲረዱ ወዲያውኑ ይሰርዙት፣ ያስወግዱት።
- በግልጊዎ (ኮምፒውተሮ) ላይ የጸረ ቫይረስ ክትብቱስ (anti-virus software) መኖሩን እርግጠኛ ይሁኑ። በአሁኑ ጊዜ በነጻ የሚሰጡ በርካታ ክትብ ቁሶች ሲኖሩ አንዳዶቹም በመጠነኛ ዋጋ አገልግሎት ይሰጣሉ። በአሁኑ ጊዜ ተቀባይነት ያላቸውና የተረጋገጡትን ከዚህ በታች ያቀረብን

ሲሆን ቃላቶቹ ላይ በመጫን ወደ ድረገጻቹ በቀጥታ በመሄድ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይቻላል፡፡

- avast!
- AVG
- AVIRA
- BitDefender
- ESET Smart Security
- F-Secure
- G DATA
- Kaspersky Lab Internet Security
- McAfee
- MacScan (for Mac users)
- Microsoft Security Essentials
- Norton Internet Security
- TrendMicro

❖ የጸዳቤ መልዕክትዎን ካነበቡ በኋላ ሁልጊዜ ከመልዕክት ሣጥንዎ ተሰናብተው ይውጡ (sign out)፡፡ በተለይም በቤተመጻህፍት፣ በኪዎስኮች፣ ወዘተ ህዝብ በአብዛኛው በሚገለገልባቸው ኀያጊዎች (ኮምፒውተሮች) ላይ የሚጠቀሙ ከሆነ ይህንን ተሰናብቶ የመውጣት ልምድ ፈጽሞ መዘንጋት የለብዎትም፡፡

❖ በአሁኑ ጊዜ ኢንሳ ከሚያካሂዳቸውና ህዝቡን ለማሳመን ከሚጠቀምባቸው ተግባራት አንዱ “የተለያዩ ቫይረሶች ኀያጊዎን (ኮምፒውተሮን) ሊያበላሽ ይችላልና ይህንን ክትብቂስ (software) ከድረገጻችን ላይ በማውረድ (download) ይጠቀሙ” የሚል መልዕክት ነው፡፡ ይህ ዜጎችን በማስፈራራት ኀያጊያቸውን ለመቆጣጠር የሚደረግ እኩይ ተግባር መሆኑን ተገንዝበው በዓለም ላይ ተቀባይነት ካተረፉትና ከላይ ከዘረዘርናቸው የጸረቫይረስ ክትብቂሶች በስተቀር በተለይ ከኢንሳ ድረገጽ ላይ ምንም ዓይነት ክትብቂስ (software) እንዳያወርዱ ይጠንቀቁ፡፡

❖ ከዚህ በተጨማሪ ግለሰቦች በተለይም በትግሉ መስክ የተሰማሩ የጸዳቤ (ኢሜይል) መቀባበያ (account) በሚከፍቱበት ጊዜ በሚታወቀው ህጋዊ ስማቸው አለመጠቀም፡፡ (ይህ ከአገር ቤት ፖለቲካዊ ይዘት ያላቸውን መልዕክት ለሚያስተላልፉም ሆነ ወደ አገር ቤት መልዕክት የሚልኩትን በተለይ የሚመለከት ነው፡፡) ከላይ የጠቀስነው አንዱና ዋንኛ ጥንቃቄ የሚሻ ማንኛውም ሰው ሊተገብረው የሚችል ቀላል ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም ከሕጋዊ ስም ይልቅ የሚጠቀሙት ስም “ድል ለኢትዮጵያ” (diletiopia@xxxx.com)”፣ “ትግሉ ፈጠነ” (tiglufetene@xxxxx.com)፣

“ወያኔ ይውደም” (weyanieyiwdem@xxxxxx.com)፣ “ነጻነት አይቀርም” (netsanetayiqerim@xxxxx.com)፣ “ግፉ በዛ” (gifubeza@xxxx.com)፣ ወዘተ የመሳሰሉ ከሆኑ አቃጣሪው የቴሌ ራውተር እንደነዚህ ዓይነት ለየት ያሉ ስሞች ስለሚታሰሩለት በእነዚህ ዓይነት ስሞች የሚመጡ መልዕክቶችን ለኢንሳ ለማቀበል ይቀለዋል። ከዚህ ይልቅ ግን በጣም የተለመዱና በሚሊዮን የሚቆጠር ኢትዮጵያዊ የሚገለገልባቸውን ትክክለኛ ስሞች መጠቀም የስለላውን ተግባር እጅግ ስለሚያስቸግረው ራስን ለመከላከል በቀላሉ የሚረዳ መንገድ ነው - የመረጃ ጫካ ውስጥ መግባት ማለት አንዱ ይህ ነው።

- በክፍል 6 ላይ በዝርዝር እንዲሁም በክፍል 9 ላይ በተወሰነ መልኩ እንደገለጽነው በአሁኑ ጊዜ በአዲሱ ቴሌ የሚሸጡት የእጅ ስልክ ቀፎዎች የቻይና ስሪት መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ቻይናውያኑ ለዘረጉት መስተጋብር በቀላሉ መረጃ ለማስተላለፍ እንዲችል ሆን ተብሎ የተፈበረከ በመሆኑ ዜጎች ራሳቸውን ለስለላ በቀላሉ እያጋለጡ ይገኛሉ። ስለሆነም እነዚህን ቀፎዎች እየተጠቀሙ የፖለቲካ ሥራ እሰራለሁ ማለት ራስን ማጋለጥ መሆኑን ሁሉም ሊረዳው የሚገባ ነው። በተቻለ መጠን በምዕራብ አገራት የሚሸጡትን የስልክ ቀፎዎች መጠቀም ወሳኝነት ያለው ነው።

በአጠቃላይ እያንዳንዱ ሰው ምን ዓይነት ጥንቃቄ መውሰድና ምን ዓይነት ብልሃት መጠቀም እንዳለበት የራሱን ጥረት ማድረግ ይገባዋል። የሚደረገው ትግል ቀላል ባለመሆኑ ራስን በተለያየ መስክ በተለይም በቴክኖሎጂ ማስታጠቅ ወሳኝነት ያለው ተግባር ነው። ባለሙያዎችን ማነጋገርና በራስ ተነሳሽነት ምርምር ማድረግም ተገቢ ነው። የዚህ ዘገባ ዋና ዓላማ ሕዝባችን ራሱን የሚከላከልበት መንገድ ማሳወቅ እንደመሆኑ ጥቃቅን የሚባሉ ጥንቃቄዎችን ባለማድረግ ስለላውን በማግዘፍ ከትግል መስክ ለመሸሽ ማሰብም አማራጭ መንገድ እንዳልሆነ ልናስገነዝብ እንወዳለን።

11. ማጠቃለያ

ቴሌን ከመነሻው ሊሸቅጠው ዳር ዳር ሲለው የነበረው የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ በቅርቡ በቦርድ ሊቀመንበሩ ዶ/ር ደብረ ጽዮን ገብረ ሚካኤል አማካይነት "መተካካት" እንደሚጀመር አረጋግጠዋል። በቴሌ የሚከናወነው መተካካት ከመገለጹ በፊት ግዙፉ የህወሃት የንግድ ተቋም የሆነው ኤፈርት ወደ ቴሌኮም ገበያ ለመሸጋገር እየተንደረደረ መሆኑ ታውቋል። በዚሁ መሰረት "ኢትዮ ቴሌኮም" (አዲሱ ቴሌ) የህወሃት/ኢህአዴግ የአፈናና የስለላ ድርጅቶች በሆኑት የደኅንነት መ/ቤት (NISS) ኢንሳና የተሸበበ፣ በንግድ ተቋሙ ደግሞ በኤፈርት የሚታለብ እንዲሆን የተፈረደበትን ሁኔታ አስመልክቶ በተለይ በኤፈርት በኩል ቴሌን ጠቅጥቀው እንዲቆጣጠሩት ስለተዘጋጁት ድብቅ ኃይሎች በማተት ሌላ ጽሁፉ ወደፊት እናቀርባለን።

የቴሌን ማኔጅመንት ለሁለት ዓመት ለማስተዳደር ኮንትራት የገባው የፈረንሳይ ቴሌኮም ቀሪ አራት ወር እያለው በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ውግዘት እየወረደበት ነው። ዋናውና ትልቁ ሽቀባ ግን "የፈረንሳይ ቴሌኮም ብቃት የለውም" በሚል የመረጃና የደህንነት ሚኒስትሩ በቅርቡ የሰጡት መግለጫ ነው። እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ በቀሪው ስድስት ወር ውስጥ በቴሌ መተካካት ይጀመራል። ልብ እንበል ማን ማንን እንዲተካ ይደረጋል?

በኢትዮጵያ ህዝብ ሃብትና ንብረት የተማሩ ውድ ዜጎች ከኃላፊነታቸውና ከስራ ገበታቸው እንዲባረሩ የተደረገው ከአንድ ዓመት በፊት ነው። "ያለ አግባብ ከስራ ተሰናብተናል" የሚሉትን ጨምሮ በሙያቸው እየተከናወነ ያለውን ድርጊት ከነመዘዙ እየጠቆሙ ያሉት ስምንት ሺህ ያህል ሰራተኞች ምን ሰበብ ሊቀርብላቸው ይሆን? "ኮንትራት የተሰጠው ድርጅት አልፈለጋችሁም" ተብለው የተባረሩት ወገኖች በመተካካቱ ልምድና ችሎታቸውን ታቅፈው ተመልካች ሆነው ሊቀሩ? ቴሌን የደህንነት አፈና ማዕከል የማድረጉ ምስጢር ፍንትው ብሎ የሚታየው እዚህ ላይ ይሆናል። የምሁራን ፍልሰት አሳሳቢ በሆነባት አገራችን "ፍለሱ፣ ሂዱ፣ ተሰደዱ ወይም እንድትሰደድ እናደርግሃለን" የሚባሉ ዜጎች የመኖራቸውን ያህል በብዛትና በጥራት እንዲማሩ፣ እንዲሰለጥኑ፣ ልምድ እንዲያገኙ ወዘተ ልዩ ትኩረት የተሰጣቸው አነስተኛ ክፍሎች አሉ - በተለይ የትግራይ ተወላጆች! እነዚህ ወገኖች አገሪቱ አለኝ በምትላቸው ተቋማት እንዲባረሩ የሚደረጉ ባለሙያዎችን ዱካ እንዲተኩ እየተደረገ የዋና ዋና ተቋማት ኃላፊና መሪ ሆነዋል። የዚህ ጽሁፍ ዋና መነሻ ሃሳብ ባለመሆኑ ዝርዝር ጉዳይ

ውስጥ ባይገባም አደጋውንና አብዛኞችን የማግለሉ ስራ ምን ያህል ገጦ የወጣ መሆኑን፣ ምስጢር እናድርገው እንኳን ቢባል ምስጢር ሊሆን የማይችልበት ተፈጥሯዊና አሃዛዊ ማጋለጫዎች ያሉት እንደሆነ ጠቁሞ ማለፉ እጅግ ውድ ጉዳይ ይሆንብናል።

የዛሬ 120 ዓመት አካባቢ አገራቸውን የማሳደግና በቴክኖሎጂ የማበልጸግ ሱስ ተጠናውቷቸው የነበረው ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ስልክ ወደ ኢትዮጵያ ባስገቡበት ወቅት መጀመሪያ የስልክ ግንኙነት ያደረጉት በቤተመንግሥታቸውና በግምጃ ቤት መካከል ነበር። የሰው ድምጽ በሽቦ ሲተላለፍ የሰሙት ካህናት ድርጊቱ **"የሰይጣን ተግባር ነው"** በማለት ከፍተኛ ተቃውሞ ሲያስነሱ ሕዝቤ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዳይሆን የምትከላከለ ከሆነ ሃይማኖቴን አቀይራለሁ በማለት እምዬ ምኒልክ በማስፈራራታቸው ካህናቱ ዝምታን እንዲመርጡ ተገድደው ነበር። የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ሲመሠረት የተፈጸመው ይህ ታሪክ አሁን እየተከሰተ ካለው ሁኔታ ጋር ስናነጻጽረው ሁኔታው ምን ያህል የተገላቢጦሽ እንደሆነ እያንዳንዱ ኢትዮጵዊ የሚያስተውለው ነው። ዓላማውም ምን ያህል በሁሉ አቅጣጫ አገርን ማፍረስ እንደሆነ ለመረዳት ብዙ ጥናትና ምርምር የሚጠይቅ አይመስልም።

የቴሌኮም ቴክኖሎጂ ካለው ውስብስብ ባሕርይ በመነሳት ቴሌን እንደሌሎች ተቋማት በቅጽበት መቆጣጠር (መውረር) ስለማይቻል ከልጅነታቸው ጀምሮ የህወሃትን ጭፍንና በዘር ላይ የተመሠረተ ፖለቲካ እንዲሁም የተጣመመ ኢትዮጵያዊነትንና የተዛባ የኢትዮጵያን ታሪክ እየተጋቱ እንዲያድጉ የተደረጉ የትግራይ ወጣቶችን በከፍተኛ ደረጃ በማሰልጠን ቴሌን እንዲረከቡ ተወጠነ። ትምህርትና ስልጠናም ተሰጠ። የምዕራብ አገር የቴሌኮም ኩባንያዎች ተጠራርገው እንዲወጡ ተደረገ። ህወሃት/ኢህአዴግ በሃያ አንድ ዓመት የአገዛዝ ዘመኑ የቴሌን ጉዳይና አጀንዳ አፈር አልብሶ በመቃብሩ ላይ አዲስ አጀንዳ ብቅ አደረገ። ቴሌ በአፍቃሪ ማኦውያን ሙሉ ፈቃድ በማኦ ልጆች ቴክኖሎጂ ታነጸ፣ በስርዓቱ ታማኞች የሰው ኃይሉ ተገነባ። የህወሃት የንግድ ተቋም የሆነውና "ትግራይን መልሶ ለማቋቋም" በሚል ተመስርቶ የኢትዮጵያን በርካታ የንግድ ተቋማት በመቆጣጠር ትግራይን እያለማ የሚገኘው ኤፈርት ቴሌን ዳር ሆኖ ሲያሽኮረምም ኖሮ በመጨረሻ "የቴሌኮም ቢዝነስ አሰኘኝ" ሲል ማዜም ጀመረ። አፈና፣ ኔትወርክና ቢዝነስ ተገጣጠሙ። በህወሃት የስለላ ድርጅት የተሸበበው እና በኤፈርት ለዘመናት ለመታለብ የተዘጋጀው አዲሱ ቴሌ የአፈና ተቋም ማለት ይህ ነው። ደኅና ሰንብት ቴሌ!

የዝግጅት ክፍሉ ማስታወሻ

በዚህ ሪፖርት የቀረበው መረጃ በኢትዮጵያችን የተካሄደውንና በመካሄድ ላይ ያለውን የአፈና መዋቅር በጥቂቱ የሚያወሳ ነው። ሪፖርቱ የህወሃት/ኢህአዴግ የደኅንነትና የአፈና ተቋማት ከቴሌኮም አገልግሎት ጋር እንዴትና ለምን እንደተቆራኙ፣ የምዕራብ አገራት የቴሌኮም ቴክኖሎጂ የተገፋበትን ምስጢርና አዲሱን ቴሌ ከአገር ወዳዶች በማጽዳት የህወሃት/ኢህአዴግን ፖለቲካና ስውር አጀንዳ ማስፈጸም ይችላሉ ተብለው ለታመነባቸው ክፍሎች ወይም የአገዛዙ "ቁሶች" እንዲዛወር የተደረገበትን ምክንያት ያሳያል ብለን እናምናለን። በመሆኑም በግርድፍ የቀረበውን መረጃ እንዳቀበሉን አገር ወዳዶች ሁሉ በተመሳሳይ ሌሎች የአገራቸውና የወገናቸው የወደፊት እጣ ፈንታ የሚያሳስባቸው ወገኖች "እኔ ላገሬ ምን ሰራሁ?" በሚል ራሳቸውን እንዲጠይቁ፣ ጠይቀውም የሚያውቁትን አስከፊ የአገዛዙ ተግባራት ለማጋለጥ ይችሉ ዘንድ የሞራል ግዴታ ውስጥ ያስገባቸዋል፤ የጎሊና ደወልም ይደውልባቸዋል የሚል የጸና እምነት እንድንሰንቅ አድርጎናል። በተለያዩ መስኮች አገዛዙ የሰዎችን የሞራልና የግል ነጻነትን በሚፈታተንና በሚዳፈር መልኩ እየፈፀመ ያለውን ህገወጥ፣ ሰብዓዊነት የጎደለው፣ ፓርቲና ወገን ሳይለይ በጅምላ የሚያራምደውን የ"ቀርጥፈህ አጥፋው" እርምጃ ለመበጣጠስ ወደውም ሆነ ተገደው አገዛዙን በማገልገል ላይ ያሉትን ሁሉ የበኩላቸውን እንዲያበረክቱ በዚህ አጋጣሚ እንጋብዛለን። አበክረንና አጠንክረን የምንጮህለት **"ከጎሣ ይልቅ ሰብዓዊነትን ይቅደም"** የሚለው የትግል መስመር ግቡን ይመታ ዘንድ፣ ከፍሬውም እኩል ተጠቃሚ ለመሆን ቅንነት የተሞላው የሁሉም ዜጎች ኩታ ገጠም አንድነት ብቸኛ መገለጫ በግድ የተጫነብንን ክፉ አገዛዝ ከውስጥም ከውጭም ስሩን መበጣጠስ ሲቻል ነውና በጸጸት ወደ ጎሊናችሁ ለመመለስ ለምትፈልጉ ሁሉ የበኩላችሁን እንድታበረክቱ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን። **እናንተ ነጻ ሳትወጡ እኛ ብቻችንን ነጻ መሆን አንችልምና** የቁራ ጩኸት ብቻውን አንዳችም የሚፈይደው ነገር ስለሌለ፣ በተግባር የአገዛዙን ገመና እርቃን በማስቀረት **"ከጎሣ ይልቅ ሰብዓዊነትን"** የሚያስቀድመው **የአዲሲቷ ኢትዮጵያ** ብስራት ይፋጠን ዘንድ የበኩላቸውን ለማበርከት፣ አስተያየትም ሆነ ተጨማሪ መረጃ ለመስጠት ወይም የተጀመረውን ግርድፍ መረጃ ለማጠናከርና ለማዳበር ለምትፈልጉ ሁሉ ከበሬታችን ታላቅ መሆኑን ከወዲሁ ለመግለጽ እንወዳለን። የሃፍረት ሠንሠለት ሽብቦ ለያዛችሁ ሁሉ ዳግም ሃፍረታችሁን በማራገፍ ለጥሪው ምላሽ እንድትሰጡ እንጋብዛለን!!

ዋቢ

http://www.insa.gov.et
http://english.eximbank.gov.cn/
http://wwwen.zte.com.cn/en/
http://www.thereporterethiopia.com/News/chinese-israli-companies-face-off-billions-of-dollars-telecom-project.html
http://www.thereporterethiopia.com/Business-Feature/the-telecom-challenge-ahead.html
http://www.ethiopianreporter.com/news/293-news/3585-2011-10-01-12-32-46.html
http://www.ethiotelecom.et/amharic/index.php
http://www.fdredefenceforce.gov.et/
http://www.waltainfo.com/
http://www.ifrc.org/
http://www.actionaid.org/ethiopia
http://www.crdaethiopia.org/index.php
http://infomedtec.com/ercs/index.php
http://googleblog.blogspot.com/2011/06/ensuring-your-information-is-safe.html
http://support.google.com/accounts/bin/answer.py?hl=en&answer=32040
http://blogs.wsj.com/digits/2011/06/02/top-10-things-you-can-do-to-protect-your-gmail-account/
www.iss.co.za/
http://www.mcit.gov.et/?q=home.aspx

የስዕል ዋቢ

[i] http://www.eprdf.org.et/web/guest/gallery
[ii] http://yle.fi/uutiset/ulkomaat/2012/03/etiopia_hyokkaa_muttei_halua_sotaa_3347594.html
[iii] http://www.eprdf.org.et/web/guest/gallery
[iv] http://www.ertagov.com/am/contact-erta-addis-ababa-ethiopia/1767-2011-12-20-18-02-37.html
[v] http://www.ertagov.com/amerta/component/content/article/49-erta-tv-hot-news-addis-ababa-ethiopia/558-16-.html
[vi] http://www.ethiopianreporter.com/politics/295-politics/5598-2012-03-17-08-58-56.html
[vii] http://www.ethpress.gov.et/ethpress/main/economy.php?economyId=466
[viii] http://www.eipo.gov.et/
[ix] http://www.federalpolice.gov.et/flashgallery/flashgallery.html

[x] http://www.newsdire.com/news/568-addis-ababa-to-get-street-surrviellance-cameras.html
[xi] http://www.addistribune.com/Archives/2001/05/18-05-01/Kinfe.htm
[xii] http://www.addisallaround.com/Home/tabid/83/default.aspx?viewId=62
[xiii] http://www.ethiotelecom.et/news/news.php?id=61
[xiv] http://www.witfor2007.org/sponsor
[xv] http://www.ethiotelecom.et/company/managemenchart.php
[xvi] http://www.orange.cm/UserFiles/Latute%281%29.jpg
[xvii] http://www.insa.gov.et/INSA/faces/news/morenews.jsp?newsid=30
[xviii] http://www.waltainfo.com/index.php?option=com_content&view=article&id=2671:opening-remark-by-dr-debretsion-gebremichael-communication-and-information-technology-minister-at-innovation-africa-digital-summit-2012-addis-ababa-march-27-2012&catid=68:speech&Itemid=296
[xix] http://www.iss.co.za/show_personnel.php?office=4